# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 323 ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የቱሪዝም ልማቶች እያንዳንዱ የዓለም ተጓዥ ኢትዮጵያን የዕቅዱ አካል አድርጎ እንዲመጣ የሚያደርጉ ናቸው

## - የሉሲ ቅሪተ አካል የተገኘበት 50ኛ ዓመት ትናንት ተከብሯል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም መዳረሻ ልማቶች እያንዳንዱ የዓለም ተጓዥ ኢትዮጵያን የጉብኝት ዕቅዱ አካል አድርጎ እንዲመጣ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

"የድንቅ ግኝት ግማሽ ምዕት ዓመት" በሚል መሪ ሃሳብ የድንቅነሽ (Lucy) ቅሪተ አካል የተገኘበት 50ኛ ዓመት መታሰቢያ በቱሪዝም ሚኒስቴር አስተባባሪነት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ትናንትና ተከብሯል።

በመድረኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ ሀብቶች በመገንዘብ መንግሥት ቱሪዝምን የሀገሪቷ ወሳኝ የኢኮኖሚ ብልጽግና መሠረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብለዋል።

የቱሪዝም ልማቶች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# መምህራን የሰላም፣ የመደማመጥና የመወያየት እሳቤ እንዲበዛ ትኩረት አድርገው ሲሠሩ ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- መምህራን የሰላም፣ የልማት፣ የመከባበር፣ የመደማመጥና የመወያየት እሳቤ እንዲበዛ ትኩረት አድርገው ሊሠሩ ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የክረምት ልዩ የመምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና መርሐ-ግብር መክፈቻን በበይነ-መረብ ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ለመምህራን የሚሰጠው ሥልጠና በትምህርት ጥራት ላይ የተጀመሩ ሥራዎችን በእጅጉ ያሳልጣል።

ሥልጠናው የፖለቲካ ሳይሆን ሙያ ተኮር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ይህም ለመምህራን የተሻለ ግንዛቤ እና እውቀት

መምህራን የሰላም፣... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በቢሾፍቱ የሚገነባውን ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በ18 ወራት ለማጠናቀቅ ታቅዷል

## - በአየር መንገዱ ላይ የሚቀርቡ ክሶች መሠረተ ቢስ መሆናቸውም ተገልጿል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቢሾፍቱ የሚገነባውን ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በሚቀጥሉት 18 ወራት ለማጠናቀቅ ማቀዱን አስታወቀ። በአየር መንገዱ ላይ የቀረቡት ክሶች መሠረተ ቢስ መሆናቸውንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸምን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ፣ የቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ማስፋፊያ እየተደረገለት ቢቆይም እየጨመረ የመጣውን ዓለም አቀፍ መንገደኛ ማስተናገድ ወደማይችልበት ደረጃ እየደረሰ ነው። ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትም አየር መንገዱ በቢሾፍቱ ተጨማሪ አየር ማረፊያ ለመገንባት እየሠራ ነው።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፣ ተጨማሪ አየር ማረፊያው የሚገነባው ቢሾፍቱ አካባቢ ሲሆን አየር ማረፊያውን ዲዛይን የሚያደርግ ዓለም አቀፍ ተቋራጭ ተመርጧል። ዲዛይኑን እና

በቢሾፍቱ የሚገነባውን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ማርሽ ቀያሪው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ

**አዲሱ ገረመው**

መንግሥት አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምን አስመልክቶ ያሳለፈውን ውሳኔ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን አስታውቋል። ከትናንት ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው ይህ ማሻሻያ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ልማትን ከማረጋገጥ እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሰነድ እንደሚያትተው፤ እስካሁን የነበረው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመንና ዝቅተኛ የዋጋ ንረት መኖሩን ለማረጋገጥ የታለመ ቢሆንም፣ በሂደት ግን ለጥቁር ገበያ መስፋፋት፣ ለከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ በከበሩ ማዕድናት

የኢኮኖሚ ማርሽ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ከ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ብሄራዊ መታወቂያ ለመውሰድ ተመዝግበዋል

## - በ364 ጣቢያዎች የምዝገባ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ብሄራዊ መታወቂያ ለመውሰድ የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር ከ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ መድረሱን የኢትዮጵያ ብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም አስታወቀ። በ364 የምዝገባ ጣቢያዎች አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑም ተገልጿል።

በኢትዮጵያ ብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ወ/ሪት ቃልኪዳን አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓትን በመዘርጋት ዜጎች እና ሕጋዊ ነዋሪዎች የመታወቅ መብታቸው እንዲረጋገጡ እና አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። በአሁኑ ጊዜም አገልግሎቱን ለሕዝቡ ተደራሽ ለማድረግ በ364 ጣቢያዎች ምዝገባ እየተካሄደ ይገኛል።

ብሄራዊ መታወቂያ አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ማግኘት ከማስቻል ባለፈ በአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር፣ በግል እና በመንግሥት ተቋማት የማንነት ማረጋገጥ ሂደት በተቀላጠፈ መንገድ እንዲከናወን የሚያደርግ ነው ያሉት ወ/ሪት ቃልኪዳን የዲጂታል መሠረተ ልማት መዘርጋትን ዋና ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ፕሮግራም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ወ/ሪት ቃልኪዳን ገለጻ፤ ምዝገባው በኢትዮጵያ ፖስታ ቤት ዋና መሥሪያ ቤት፣ የቤተ መንግሥት ፓርኪንግ ፣ በገቢዎች ሚኒስቴር በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት፣ በኢትዮ-ቴሌኮም እንዲሁም በምዝገባ አጋሮች በተለይም በአዲስ አበባ በዘጠኝ ባንኮች ምዝገባ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በክልል ከተሞች የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ በገቢዎች ቢሮዎች በኩል እንዲሁም በኢትዮ-ቴሌኮም የምዝገባ ጣቢያ አማካኝነት እየተከናወነ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

ወ/ሪት ቃልኪዳን፤ ወደ ፊት ሁሉም ዜጎች ወደዚህ ሥርዓት እንደሚገቡ ጠቀሙው፤ የምዝገባ ሥርዓቱ በራስ አቅምና አብረው ከሚሠሩ አጋር አካላት ጋር እንዲሁም አቅም ባላቸው የግል ድርጅቶች አማካኝነት የሚከናወን እንደሆነም ጠቁመዋል። የቴክኖሎጂ ሥርዓቱ በራስ ባለቤትነት የሚተዳደርና ለጥቃት የማይዳርግ ጠንካራ ጥበቃ የሚደረግለት እንደሆነም አመላክተዋል።

የብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሥር ከመደራጀቱ በፊት በተለያዩ ተቋማት ሥር የነበረ ሲሆን፤ ልማቱ ታምኖበትና የተሻለ ውጤት ለማምጣትና በሁሉም ሴክተሮች ላይ ለመተግበር በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሥር ተደራጅቶ ሰፊ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል።

በ2015 ዓ.ም አገልግሎቱን ለማግኘት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች መመዝገባቸው የሚታወስ ነው።



አቶ መኩሪያ መርሻዬ

# የኮሪደር ልማቱ የከተማዋን ቱሪዝም ለማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው

**መዓዛ ማሞ**

ሃዋሳ፡- በሃዋሳ ከተማ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ሥራ የቱሪዝሙን እንቅስቃሴ የሚያሳድግ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ ገለጸ።

የሃዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ መኩሪያ መርሻዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በቅርቡ በከተማዋ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ሥራ የከተማዋን ገጽታ የሚቀይር ነው።

የኮሪደር ልማቱ የመንገድ ማስዋብ ሥራዎችን ያካተተ፣ የብስክሌት እና የእግረኛ መንገዶችን የለየ እና አካል ጉዳተኞችን ከግምት ባስገባ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸው ሲጠናቀቅ ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት በመስጠት ከተማዋን የሚጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ቱሪዝሙን ብሎም ኢኮኖሚን በማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

በከተማዋ በኮሪደር ልማት ሥራ በሁለት መልኩ ሥራዎች መጀመራቸውን የተናገሩት ከንቲባው፤ ሥራዎቹ በማስፋፊያ አካባቢ የሚሠሩ እና በመሀል ከተማ የሚከናወኑ ሶስት መሠረታዊ መንገዶችን ያካተቱ መሆኑን ጠቁመዋል።

የማስፋፊያ ሥራው 34 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑ 10 ትልልቅ መንገዶችን የሚሸፍን መሆኑን ጠቁመው በሥራው በመጀመሪያ ዙር 813 ተነሺዎችን ካሣ ከፍሎ የማንሳት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አመላክተዋል።

በመሀል ከተማ የሚሠሩት 7 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑት ሶስት መሠረታዊ መንገዶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመው የመንገዶቹን ደረጃ የማሻሻል ሥራዎች ይከናወናሉ ብለዋል።

መንገዶቹ ከሃይሌ ሪዞርት የቀድሞ ማዘጋጃ ፣ ከመምቦ ካፌ ሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና ከዲኤምሲ ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ እስከ ጥቁር ውሃ መግቢያ ያሉት መሆናቸውን የገለጹት ከንቲባው የመንገዶቹን ደረጃ የማሻሻል፣ የእግረኛ፣ የብስክሌት እና የአካል ጉዳተኞች መንገዶች፣ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶችን እና ፋውንቴኖችን እንዲያካትቱ በማድረግ እንደሚለሙ ተናግረዋል።

ከዲኤምሲ እስከ ሃዋሳ ሴራሚክስ ፋብሪካ ያለው የመንገድ ልማት በአካባቢው ባሉ ተቋማት እንደሚለማ አመላክተው ተቋማቱ መንገዱን ለማልማት በግምት እስከ አንድ ቢሊዮን ብር እንደሚያወጡ ገልጸዋል።

የሥራው የመጀመሪያ ምዕራፍ ከሶስት እስከ አራት ወራት ባለው ጌዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ያሉት ከንቲባው ሁለተኛ ምዕራፍ ሥራዎች የሚጀመርባቸው ቦታዎችም ጥናት እየተደረገባቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

ሥራው የሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታል ወጪዎችን እንደሚጠይቅ ገልጸው የሕዝብ ተሳትፎን እና ተቋማት የሚያለሙትን ጨምሮ እስከ 3 ቢሊዮን ብር ወጪ እንደሚገመት ገልጸዋል።

እንደ ከንቲባው ገለጻ የከተማዋ ነዋሪዎች የኮሪደር ልማት ሥራውን በሃሳብ፣ በገንዘብ እና በሞራል እየደገፉ ነው። የተጀመረው የልማት ሥራ የከተማ አስተዳደሩ ትልቅ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመው ሁለት ኮሚቴ ተዋቅሮ በከፍተኛ ክትትል ሥራው በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

# በ2017 ጎንደር ከተማን `ስማርት ሲቲ` ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እየተሠራ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

ጎንደር፡- በ2017 ጎንደር ከተማን `ስማርት ሲቲ` ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እየተሠራ መሆኑን የከተማዋ ከንቲባ ተናገሩ።

የጎንደር ከተማ ከንቲባ አቶ ባዩህ አቡሀይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በከተማዋ በተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ማንሠራራት ጀምረዋል።

በከተማዋ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውን ወደነበረበት ለመመለስ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ከንቲባው በተያዘው በጀት አመትም ከተማዋን `ስማርት ሲቲ` ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን እየተሠራ ነው ብለዋል።

እስካሁን በነበረው ሂደት መከላከያ ሠራዊት፣ የአካባቢው የጸጥታ ኃይልና ማህበረሰቡ በሰሩት የቅንጅት ሥራ በከተማዋ አንጻራዊ ሰላም ከመስፈኑም ባለፈ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ከነበሩበት ማንሠራራት እንደጀመሩ ተናግረዋል።

በአካባቢው በተፈጠሩ ችግሮች ከወልቃይትና በዙሪያው ካሉ አካባቢዎች የንግድ ትስስሩ ተስተጓጉሎ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን በተገኘው አንጻራዊ ሰላም ምርትና ሸቀጦች ወደ ከተማው እየገቡ በመሆኑ የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ከነበረበት መፋዘዝ ወጥቶ መነቃቃቱን አስታውቀዋል።

ባለፉት ዓመታት የተፈጠሩት ሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች የከተማዋን አጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሲያስተጓጉል መቆቱን አስታውሰዋል።

እንደ ከንቲባው ገለጻ፤ ከቱሪዝም ዘርፉ በዓመት ከ160 ሺህ እስከ 200 ሺህ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ከተማዋን እንደሚጎበኙና በዚህም ከትኬት ሽያጭ ብቻ ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ በቀጥታ ይገኝ ነበር።



ፎቶ ኢዮብ ተፈራ

አቶ ባዩህ አቡሀይ

በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ በዘንድሮው ዓመት ሁለት ሺህ የሚሆኑ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ብቻ ወደከተማዋ መምጣታቸውን ገልጸው፤ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች በመቀነሳቸው ባለፉት ዓመታት ለከተማዋ፣ ለክልልና ለሀገር ኢኮኖሚ ይገኝ የነበረው ገቢ መቀነሱን አብራርተዋል።

የግጭት ትርፉ የሀገርን እድገት ማቀጨጭ፣ ማክሰርና ማጥፋት ነው ያሉት ከንቲባው፤ ይህንን ለመቀልበስ እንደከተማ ሰፊ ሥራ ሥንሰራ በመቆየታችን፤ አንጻራዊ ሰላም ማስፈን ተችሏል ብለዋል። በቀጣይ የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ወደ ሙሉ ሰላም ለመቀየር ከፌዴራል ጀምሮ በሁሉም ደረጃዎች በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አንስተዋል።

በስምንት ቀጣና ሕዝቡን በማወያየትና የሰላም ካውንስል በማቋቋም ግጭቶችና ችግሮች በውይይትና በድርድር እንዲፈቱ አቅጣጫ መቀመጡን አመላክተዋል።

የተቀመጠውን አቅጣጫ ስኬታማ ለማድረግ ጫካ የገቡ አካላት ችግራቸውን ለውይይትና ለድርድር በማቅረብ የከተማው ነዋሪ የተሟላ ሰላም አግኝቶ እጁን ወደ ልማት እንዲመልስ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት ሕዝቡን ያማረሩ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት ከደሴ ከተማና ከዙሩን ችሎት ተሞክሮ በመውሰድ የከንቲባ ችሎት መድረክ ተጀምሮ ለረጅም ዓመታት የቆዩ ችግሮችን መፍታት እንደተቻለ ገልጸዋል።

ጎንደር ከተማ ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንትና ለቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹ መሆኗን ገልጸው፤ በቀጣይም የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ወደተሟላ ሰላም በመቀየር ሕዝቡን ያሳተፈ የሰላም ግንባታና የልማት ሥራዎች እንደሚከናወኑ አስታውቀዋል።

የከተማዋን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ማነቃቃት፣ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፣ ከተማዋን ስማርት ሲቲ ማድረግ እና ዘላቂ ሰላም ማስፈን የ2017 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫ መሆናቸውን ተናግረዋል።

# በክልሉ ለሚደረገው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ ሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**



ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል እየተከናወነ ለሚገኘው የአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ የነቃ የሕዝብ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚገባ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በጋምቤላ ክልል የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከወከሉ ተመራጮች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረክ በትናንትናው ዕለት ማካሄድ ጀምሯል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም በመድረኩ መክፈቻ ላይ እንደገለፁት፤ ኮሚሽኑ በምክክር ሂደቱ ብዙ ርቀቶችን በመጓዝ መቋጫው በሆነው ለምክክር አጀንዳ ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦች በመሰብሰብ ላይ ይገኛል።

በዚህም በመዲናዋ የአጀንዳ ልየታ የምክክር ምዕራፍ መካሄዱን እንዲሁም ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አጀንዳ መሰብሰብ ሂደት ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የጋምቤላ ክልል ነዋሪዎችም በመጪዎቹ ቀናት በሚደረገው የምክክር እና የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል ብለዋል።

የምክክር ሂደቱ ሁሉን አካታች እና አሳታፊ፣ ተዓማኒና ግልጽ የሆነ አሠራር እንዲኖረው ሰፊ ቅድመ ዝግጅት ሲሠራ የነበረ መሆኑን ገልፀው፤ ተሳፊዎቹ ለሀገር አንድነት የሚበጁ ሃሳቦችን በማንሳት የሚመካከሩበት እና የአጀንዳ ሃሳቦቻቸውን የሚያዘጋጁበት መድረክ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ በጋምቤላ ክልል ባዘጋጀው በዚህ የአጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ የሲቪክ ማህበራትን ጨምሮ በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ከአንድ ሺህ 300 በላይ ተወካዮች እንደሚሳተፉም ገልፀዋል።

ኮሚሽነር መላኩ እንደገለፁት፤ በመርሃ ግብሩ ሶስት ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን ተሳታፊዎች በምክክርና በውይይት የአጀንዳ ሃሳቦችን ማምጣት፤ አጀንዳዎቻቸውን የጋራ ማድረግና ማዳበር እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳቦችና የማጠቃለያ አጀንዳ መስጠት የመርሃግብሩ አካል ናቸው።

በሂደቱ መጨረሻም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለሀገራዊ ምክክር ጉባዔ ተሳታፊ የሚሆኑ ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ ብለዋል።

በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚሰበሰበው አጀንዳም እጅግ መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሕዝቡ መፍትሄ ማግኘት አለባቸው የሚለውን ሀገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ያነሳል ተብሎ እንደሚጠበቅም ጠቅሰዋል።

በመሆኑም ኮሚሽኑ እያከናወነ ያለው የምክክር ሂደት ሁሉንም ያሳተፈ በመሆንና ለችግሮች መፍትሄ በማስቀመጥ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ የሚያስችል ትልቅ ምዕራፍ በመሆኑ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በመድረኩ ላይ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ መምህራን እና የሀገር ሽማግሌዎች እየተሳተፉ ይገኛል።

# የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ዳግም መመዝገብ ለምን አስፈለገ?

**ማርቆስ በላይ**



በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ጥራት ላይ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት መንግሥት የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። እየተወሰዱ ካሉት ስትራቴጂዎች መካከል ተቋማትን በአዲስ አሠራር መመዝገብ አንዱ ነው። ታዲያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ዳግም መመዝገብ ለምን አስፈለገ?

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለጹት፤ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚወሰዱ ርምጃዎች በርካታ ውጤቶችን እያስገኙ ነው።

የመውጫ ፈተና ውጤት የትምህርት ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ጉዳይ በመሆኑም የዘንድሮው ዓመት የመውጫ ፈተና የግል ኮሌጆች ያስመዘገቧቸው ውጤቶች ለሕዝብ ይፋ መደረጋቸውን የገለጹት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ዘንድሮው የመውጫ ፈተና ከ382 በላይ የግል ኮሌጆች መካከል 202 ኮሌጆች ተማሪዎቻቸውን አስፈትነዋል ብለዋል። በግል ኮሌጆች 95 ሺህ 465 ተማሪዎች ለፈተና የተመዘገቡ ሲሆን 68 ሺህ 163 ተማሪዎች ፈተናውን ወስደዋል ሲሉ ይገልጻሉ።

ሚኒስትሩ አክለውም፤ የግል ከፍተኛ ትምህርት በዘንድሮው የመውጫ ፈተና ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች 13 በመቶ ያሳለፉ ሲሆን 22 የግል ኮሌጆች ምንም ተማሪ አላሳለፉም። በተጨማሪም 25 በመቶ ተማሪዎችን ማሳለፍ የቻሉት 29 የግል ኮሌጆች ብቻ መሆናቸውን ይናገራሉ።

በመንግሥት ኮሌጆች 94 ሺህ ተማሪዎች ተመዝግበው 88 ሺህ 94 ተማሪዎች ፈተናውን መውሰዳቸውን በመግለጽ፣ ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል 58 በመቶ ማሳለፋቸውን ይገልጻሉ።

በቀጣይ በምስጢራዊ ህትመት አማካኝነት ትምህርት ሚኒስቴር ዲግሪ ያሳትማል። የግል ትምህርት ተቋማት ዲግሪ ማሳተም ያቆማ ሲሉም ጠቁመዋል።

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፣ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለትርፍ የሚሠሩ ቢሆንም በኢትዮጵያ ልጆች ላይ ችግር በሚፈጥር መልኩ መሆን የለበትም። አዲሱን ትውልድ ዓለም ውስብስብ እየሆነ በሚሄድበት ዘመን ሳይማሩ የሚመረቁበት ሁኔታ መቆም አለበት።

የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ሽፈራው ሽጉጤ በበኩላቸው፤ በግሉ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማትን በመመሪያ ላይ ተመስርቶ እንደገና ለመመዝገብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ተቋማቱ አዲስ የትምህርት ፕሮግራምና የትምህርት ተቋም እንዳይከፍቱ ፍቃድ ተከልክሎ ቆይቷል። ምክንያቱም መመሪያን፣ አሠራርን፣ የትምህርት ጥራትን ፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትን ማሳለጥ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት መሆኑን ይገልጻሉ።

የተቀመጡት መስፈርቶች የትምህርት ጥራትን፣ ተጠያቂነትን፣ በሕዝቡ፣ በተቋማትና በተማሪዎች መካከል ያሉ ስጋቶችን በሚያስወግድ መንገድ እንደሚተገበርና በትምህርት አሠጣጥ ሥርዓት ላይ የነበሩ ችግሮችን ማስወገድ በሚችል መልኩም መዘጋጀቱን ይናገራሉ።

እያንዳንዱ ተቋም የተማሪዎቹን ፣ የመምህራኑን፣ የአሠራሩን የመማሪያ ማስተማሪያ ተቋማቱን መረጃዎቹን በተሟላ መንገድ ያቀርባሉ። ለምዝገባው ለአንድ ወር የዝግጅት ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን እስከ ታህሳስ 30 ሁሉም እንደገና እንደሚመዘገቡም ያስረዳሉ።

መመሪያው መስፈርት ያሟሉ፣ የመግቢያ ነጥብ፣ ዲግሪ ደጋግሞ በማተም፣ የተማሪዎችን መብት በመግፋት የነበሩ ችግሮች በሚፈታ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉ ይገልጻሉ።

አንድ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በመውጫ ፈተና 25 በመቶ ተማሪዎችን ካላሳለፈ ድጋሚ ፈቃድ ሊያገኝ አይችልም። በመመሪያው የግሉን ብቻ ሳይሆን የመንግሥትንም የሚመለከት ቢሆንም በስፋት በግሉ ዘርፍ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ የታሰበ እንደሆነ ያስረዳሉ።

እስካሁን በሥራ ላይ ያለው ምዝገባ የትምህርት ጥራትን፣ ግልጸኝነትን፣ የተማሪዎች ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል አይደለም። በዚህም መሠረት የመመዝገቢያ ሕግ የተዘጋጀ ሲሆን ሁሉም ተቋማት መብታቸው እንዲጠበቅ፣ ተጠያቂነታቸው እንዲረጋገጥና የትምህርት ጥራትን ለማምጣት እንደሚያስችል ይገልጻሉ።

በባለሥልጣኑ የከፍተኛ ትምህርት ፍቃድ አሰጣጥ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሕይወት አሰፋ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ በባለሥልጣኑ እንደሀገር ያሉ የመንግሥት፣ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ድጋሚ ይመዘገባሉ።

ለምዝገባው ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመጀመሪያ በሁለተኛ ዲግሪ፣ በርቀት ትምህርት፣ በበይነ መረብ፣ በድንበር ተሻጋሪ መርሃግብሮች ላይ ዘጠኝ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል። በመመሪያ ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት፣ የመምህራን ትምህርት ደረጃ፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ መሠረታዊ ግብዓቶች፣ የመማር ማስተማሪያ ህንጻዎችን ማሟላት እንዳለባቸው ተቀምጧል ሲሉ ያስረዳሉ።

በመመሪያው የህክምና ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመክፈት መሠረታዊ ግብዓቶችን ያሟላ የማስተማሪያ ሆስፒታል ሊኖረው እንደሚገባ ተቀምጧል። በተጨማሪም የሕግና መምህርነት ዘርፎች ለግል ዘርፉ አለመፈቀዳቸውንም ይገልጻሉ።

አሠራሩ ተግባራዊ ሲሆን ተማሪዎች ተቋማትን መርጠው እንዲገቡ ያስችላል። መመሪያው ተቋማቱም የትምህርት ጥራትን በማምጣት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በር ከፋች መሆኑን አመላክተዋል።

# በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆት ከ64 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት ደርሷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆት ከ64 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት መድረሱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አበበ ተስፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆትና ተያያዥ ወንጀሎች ከአመት አመት እየጨመሩ ነው።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆት ከ64 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት ደርሷል ብለዋል።

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠረው የጸጥታ ችግር ለስርቆት ወንጀሉ ከአመት አመት መበራከት ዋነኛ መንስኤ መሆኑን አስረድተዋል።

ባሳለፍነው በጀት ዓመት ብቻ በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ በተፈጸመ ሥርቆትና ተያያዥ ወንጀሎች ከ64 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት ደርሷል ያሉት አቶ አበበ፤ ከ2015 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸርም የስርቆት ወንጀሉ ከፍተኛ ብልጫ እንዳለው ጠቁመዋል።

አቶ አበበ አክለውም፤ በ2016 በጀት ዓመት የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆትን ጨምሮ በአጠቃላይ 314 ወንጀሎች ተፈጽመዋል ያሉ ሲሆን ወንጀሎቹ በብዛት የተፈጸሙት በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና አማራ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ነው ብለዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆት እና በተቋሙ ሠራተኞች የሚፈጸም የገንዘብ እምነት ማጉደል በበጀት ዓመቱ ከተፈጸሙ ወንጀሎች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውንም ነው አያይዘው ያብራሩት።

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ ከወንጀሉ ጋር ተያይዞ የተጠረጠሩ 71 ግለሰቦች ላይ ከአምስት ወር እስከ 18 ዓመት የሚደርስ እስራትና የገንዘብ ቅጣት በፍርድ ቤት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል።

ኤሌክትሪክ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት መሠረት ነው ያሉት አቶ አበበ፤ በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ የሚፈጸም ስርቆት በተቋሙ ላይ ከሚያደርሰው የገንዘብ ጉዳት በተጨማሪ የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በመግታት ወደ ውስብስብ ችግር ሊያስገባ የሚችል ነው።

ችግሩን ለመቅረፍ በየአካባቢው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አበበ፤ ህብረተሰቡ ኤሌክትሪክ ለሀገር እድገት ያለውን ሚና በመገንዘብ እንዲጠብቅና የስርቆት ወንጀል ሲፈጸም ጥቆማ በማድረግ እንዲተባበር ጥሪ አቅርበዋል።

በተቋሙ በኩል ችግሩን ለመከላከል የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን ጠቅሰው፤ በተለይ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ግንዛቤ በማስጨበጥ ረገድ ሰፋፊ ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

# የኢኮኖሚ ማርሽ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለሚደረግ ሰፊ የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ከባንክ ሥርዓት ውጭ እንዲሆንና ከሀገር እንዲሸሽ አንዱና ዋነኛ ምክንያት ሆኗል።

ይህ ሁሉ ከአምራች ዘርፎች ይልቅ ጥቂት ሕገወጦችና ደላሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ሥር የሰደደ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲከሰት አድርጓል። በዚህ የተነሣ በርካታ የንግድ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ተጎጂ ሆነዋል፤ የወጪ ንግድንና የፋብሪካ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ጥረቶችን ውጤታማነት ሸርሽሮታል። ከዚህ አንጻር የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ምንም ያህል ቀላል ባይሆንም አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምህረቱ በሰጡት ማብራሪያ፤ ከትናንት ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ታሪካዊ ለውጥ ሲሆን፤ ይህም ኢትዮጵያን በገበያ ላይ የተመሠረተ ተወዳዳሪ ወደሆነ የውጭ ምንዛሬ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራትና በኢኮኖሚው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውንና ሥር የሰደደውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚያሻሻልም ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ማሞ ማብራሪያ፤ ማሻሻያው ተግባራዊ የሚደረገው በአዲሱ የውጭ ምንዛሬ መመሪያ መሠረት ሲሆን፤ ይሄም መመሪያ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ በርካታ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያዎችን አሻሽሏል። ተበታትነው የነበሩ የተለያዩ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያዎችን በአንድ ላይ አጠቃሏል።

የአዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ አበይት ለውጦችና ይዘቶችን ሲያብራሩ እንደገለጹት፤ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል በሚደረጉ መስተጋብሮች ወደሚወሰንበት የገበያ ሥርዓት ይሸጋገራል። በዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚና የተረጋጋና ጤናማ የውጭ ምንዛሬ ግብይት ሥርዓት መስፈኑን በማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ይሆናል።

ከዚህ ቀደም በተለይም ባሉት 30 ዓመታት የወጡ ተበታትነው የነበሩና ያልተጣጣሙ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተሻሽለው፣ ተጣርተው፣ ተጣጥመውና ተናበው በአንድ ጥቅል መመሪያ ሥር እንዲካተቱ ሆኗል። አዲሱ ወጥ መመሪያ ለሁሉም ሰው በቀላሉ ተደራሽ ሊሆን የሚችል ነው። ከእንግዲህ ወዲያ የውጭ ምንዛሬን ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ አይኖርም። በዚህ መሠረት ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሬ ለራሳቸው ማስቀረት ይችላሉ። ይህም ለግሉ ዘርፍ የሚሠጠውን የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት በእጅጉ እንደሚያሻሽል ይታመናል። ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረው 40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን በሂደት ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ገበያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው የሚያስቀሩበት አሠራር ይዘረጋል።

የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የንግድ ሥርዓቱ ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም ሰነዱ አትቷል።

“በአሁኑ ወቅት፣ ኢትዮጵያ ከታላላቅ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎችና በማደግ ላይ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት መካከል የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ሥርዓትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያለባት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ከሕዝብ ብዛት፣ ከሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ከተመጣጣኝና ከተወዳዳሪ ግብዓቶች (የሰው ጉልበት፣ መሬት)፣ ከተጠናከረ የአየር ትራንስፖርትና ከተሻሻለ ሎጂስቲክስ፣ ከኃይል አቅርቦት፣ ከተፈጥሮ ሀብትና ከማዕድናት አኳያ በብዙ መልኩ ለኢንቨስትመንት ምቹና ሳቢ ሀገር ብትሆንም፣ እነዚህ ሁሉ ዕድሎች በአስቸጋሪና ጥብቅ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ምክንያት ውጤታማነታቸው የተጠበቀውን ያህል አልሆነም። ስለዚህ፣ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ለውጭ ኢንቨስተሮች ማነቆ ሆኖ የቆየውን አሠራር ለማስወገድና ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ይጠቅማል” ሲል የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መረጃ ያብራራል።

በሌላ በኩል የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ በኢኮኖሚው ውስጥ ኢ-መደበኛነትንና ሕገ ወጥነትን ሲያበረታቱ የቆዩ በርካታ የንግድ አሠራሮችን ለማስቀረት እንደሚረዳ ተጠቅሷል። አሁን ያለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማዕቀፍ የውጭ ምንዛሪ በባንኮች በኩል እንዲመጣ የማያበረታታና የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያፈሩ ኩባንያዎች ወይም ግለሰቦች የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ እንዲያሸሹ የሚያደርግ ነው በማለት፤ በውጭ ምንዛሪ የሚካሄድ ኢ- መደበኛ ገበያ እየተስፋፋ በመምጣቱ አብዛኛው የንግድ ማህበረሰብና የሐዋላ ተገልጋዮች በጥቁር ገበያ ሲገዙና ሲሸጡ እንደሚስተዋል አንስቷል። አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ይህንን የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና እንዲህ አይነቱን ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ እንደሆነ ነው የተገለጸው።

በጥቅሉ፣ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ ርምጃዎችን ለማጠናከር እንደሚረዳ ተመላክቷል።

ለፖሊሲው ስኬታማነት የሚወሰዱ ርምጃዎች ሰፊ በቂ ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገ የተገለጸ ሲሆን፤ በዚህም በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል መንግሥት ከውጭ የሚገቡ የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎም መወሰኑን፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ የዋጋ ንረት ምክንያት የእውነተኛ ገቢያቸው ዋጋ ለተሸረሸረባቸው ወገኖች የገንዘብ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው፤ እንዲሁም የመንግሥትን የማህበራዊ ወጪ ለመደገፍና ለውጭ ዕዳ ክፍያ የሚውለው ከፍተኛ የብር ወጪ ሌሎች ወጪዎችን በማይሻማ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ የውጭ ዕዳ ማቅለያ ርዳታ መገኘቱ ተገልጿል።

የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሑሩ ቆስጠንጢኖስ በርኽተስፋ (ዶ/ር)፤ ማሻሻያው እንዲደረግ ከ27 ዓመታት በፊት ስንነጋገርበት የነበረ ጉዳይ ነው ይላሉ። ይህ ፖሊሲ ያደጉ ሀገራትና ከአፍሪካም እንደነ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ የመሳሰሉ ለኢትዮጵያ በቅርብ ርቀት ላይ ያሉ ሀገራት የሚከተሉት ነው በማለት፤ ይህ የፖሊሲ ማሻሻያ መደረጉም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ እመርታ እንሚፈጥር ይጠቅሳሉ።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ማብራራሪያ፤ ሰው መገበያየት ሲጀምር ከካፒታል ገበያና ከውጭ ባንክ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት በመሆኑ በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይህም የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት አቅም ይጨምራል።

ማሻሻያው ጥቁር ገበያውን ለመከላከል ትልቅ ፋይዳ እንዳለው በመጥቀስ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግሥት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን በተለይ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጣውን ገንዘብና ወርቅ የመሳሰሉትን ማስቆም እንዳለበት ጠቁመዋል። ከዚህም ባሻገር ኢንቨስተሮች በስፋት እንዲገቡ ሠላምና መረጋጋት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንዳለበት መክረዋል። ይህ ከሆነ ማሻሻው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ ፋይዳ ያለው እንደሆነ ነው ያመላካቱት።

ማሻሻያው ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ልማትን ለማረጋገጥና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ኢኮኖሚውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲጠቀምበት በሚችል መንገድ ሊያራምደው እንደሚችል ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ እንዲህ አይነት ወጥ የፋይናንስ ፖሊሲ ያልነበራት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብሔራዊ ባንክ እንደ ግምጃ ቤት ሲያገለግል መቆየቱን አንስተዋል። ከነባሩ ፖሊሲዎች ሲጠቀሙ የነበሩትም ጥቂቶች ብቻ እንደነበሩ ገልጸዋል። “አሁን ላይ የውጭ ምንዛሬ ግብይቱ ይረጋጋል። በቀጣይም ካፒታል ገበያው በሰፊው እንዲንቀሳቀስ ይደረጋል። የውጭ ባንኮችም ይገባሉ። መንግሥት ሕገ ወጥ ንግድ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ሲችል ወደ ውጪ የሚላከው ምርት እያደገ ይሄዳል። የወጭ ገቢ የንግድ ሚዛን ተመጣጣኝ ይሆናል። ወደ ውጭ የሚላክ ምርት ሲያድግ፣ ሕዝቡ በከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲሠማራና የተሻለ ገቢ የሚያገኝበት መንገድ ይፈጠራል። ይህ የሀሪቷን ኢኮኖሚ ያሳድጋል” ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ብሔራዊ ባንክ ትንበያ፤ በማሻሻያ ርምጃዎቹ ምክንያት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በ 8 በመቶ ያህል ያድጋል፤ የዋጋ ንረት ወደ 10 በመቶ የተጠጋ ይሆናል፤ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ ይደርሳል፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ ይላል፤ የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ያድጋል፤ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ 8 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ይላል፤ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ከ10 ቢሊዮን ዶላር ( የ3.3 ወራት የገቢ ሸቀጦችን ወጪ ለመሸፈን የሚበቃ) በላይ ይሆናል። እነዚህ ትንበያዎች በቀጣይ ዓመታት ከላይ በተጠቀሱት ማሻሻያዎች ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የኢኮኖሚ ሽግግር ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸው።

# በቢሾፍቱ የሚገነባውን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግንባታውን የሚሠሩት ሥራ ተቋራጮች በሚቀጥሉት 18 ወራት እንዲያጠናቅቁ ስምምነት ላይ ተደርሶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

አየር ማረፊያው የሚገነባበት ቦታ ላይ ያረፉትን አርሶ አደሮች ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር የሚያስችል ቦታ በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ተለይቶልናል ያሉት አቶ መስፍን፣ የተለየው ቦታ ላይ ኑሯቸውን የሚመሩበት መኖሪያ ቤት የሚገነባ ሥራ ተቋራጭ በመመረጡ ሰሞኑን እንፈራረማለን ብለዋል።

የሲኤንኤን ናይሮቢ ጋዜጠኛ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሶማሊያ ዜግነት ያላትን መንገደኛ በማስነሳት ወንበሯን ለኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን በመስጠት በኃይል አስወርዷታል ሲል በቪዲዮ ጭምር አያይዞ ማሰራጨቱን ያስታወሱት አቶ መስፍን፣ ይህንን ክስ አንቀበለውም ፤ ትክክለኛም አይደለም ብለዋል።

እውነታው መንገደኞቹ ሶስት ሲሆኑ፤ የኢትዮጵያ ባለሥልጣን በቦታው አልነበረም። ከጎረቤት ሀገር የመጡ ቪአይፒ ቢኖሩም የተሳፈሩት በቢዝነስ ክላስ ነው። እነሱ ደግሞ የያዙት የኢኮኖሚ ክላስ ትኬት ነው። አውሮፕላን ውስጥ የገቡትም ያለፈቃድ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የተሳፋሪዋን ወንበር ለሌላ ተሳፋሪ አሳልፎ የሰጠበት ምንም ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጧል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ አየር መንገዱ እውነተኛ መረጃ ለጋዜጠኛው ለመስጠት ጥረት ቢያደርግም ፈቃደኛ ሊሆን አለመቻሉን ጨምረው ገልጸዋል።

አየር መንገዱ ዓለም አቀፋዊ ሕግን ተከትሎ የሚሠራ፣ መንገደኞችን እንደ አመጣጣቸው እና አመዘጋገባቸው የሚያስተናግድ ሲሆን፤ በቀጣይም ይህንኑ ተግባራዊ ያደርጋል ብለዋል።

በሌላ በኩል የኤርትራ ሲቪል አቬሽን ባለሥልጣን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመስከረም 30 ጀምሮ እንዳይበር የሚል ደብዳቤ መላኩን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመው፤ ደብዳቤው ይህንን አጥፍታችኋል የሚል ምንም ዓይነት ማብራሪያ አልነበረውም ብለዋል። በቀጣይ ቀን ግን በማህበራዊ ሚዲያ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትክክለኛ ያልሆነ አሠራር በመከተሉ፣ የሚጠይቀው የትኬት ዋጋ በመወደዱ፣ የመንገደኞች ሻንጣ የሚጠፋ፣ የሚሰበርና የሚሰረቅ በመሆኑ አግደነዋል እና ጉዟችሁን አስተካክሉ የሚል መግለጫ አውጥቷል ሲሉ ጠቁመዋል።

በረራ አቪየሽኑ መቋረጡ ሳያንስ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ስም የማጥፋት ሥራ የሠራ በመሆኑ ክሱ በፍጹም ተቀባይነት የለውም ሲሉ ገልጸው፤ መጋቢት ወር ውስጥ የኤርትራ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኞች ሻንጣ የሚያጉላላ በመሆኑ ለደንበኞቹ ካሳ እንድንከፍል በጻፈልን ደብዳቤ መሠረት ወዲያውኑ የማስተካከያ ርምጃ ወስደናል ብለዋል።

በወሰድነው ርምጃም መንገደኞች ከሻንጣቸው ጋር እኩል እንዲሄዱ እና በየአውሮፕላኑ ያለውን የተሳፋሪ ቁጥር በመቀነስ ችግሩ ተፈትቷል። ይህ እንደመወንጀያ መደረጉ ተገቢነት የለውም ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስህተቶችን ለማረም ዝግጁ በመሆኑ በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ጤናማ ግንኙነት፣ ንግድና ቱሪዝም እንዲኖር የሚጥር ተቋም በመሆኑ በረራው እንዳይቋረጥ የኤርትራ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናትን ለማነጋገር ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በሌላ በኩል አየር መንገዱ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 7 ነጥብ 02 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን ጠቅሰው፤ የተገኘው ገቢ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር 14 በመቶ አድጓል ብለዋል።

በጀት ዓመቱ 17 ነጥብ አንድ ሚሊዮን መንገደኞችን ማጓጓዙን ገልጸው፤ ከነዚህ ውስጥ 13 ነጥብ 4 ዓለም አቀፍ መንገደኞች ሲሆኑ ቀሪዎቹ የሀገር ውስጥ መንገደኞች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በጭነት 754 ሺህ 681 ቶን ማጓጓዙን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ስድስት በመቶ አድጓል ብለዋል። በበጀት ዓመቱ አምስት ዓለም አቀፍ የመንገደኛ መዳረሻዎችን በመጨመር የዓለም አቀፍ በረራ መዳረሻዎችን 139 ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል።

# የቱሪዝም ልማቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግም በተጠናከረ ሁኔታ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ ከተፈጥሮ ጋር የተጣጣመና ዘላቂ ገቢ የሚፈጥሩ መዳረሻዎችን አልምተናል ሲሉ አስረድተዋል።

ጥረቶቻችን የቱሪዝም ዘርፉ ዘለቄታዊ ገቢ ለማረጋገጥ ያለንን አቋም ማሳያ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ታሪኮችንና ቅሪቶችን፣ ዕምቅ ባህላዊና ታሪካዊ እንዲሁም የተለያዩ መስህቦችን ማግኘት ይችላሉ፤ በመላው ዓለም የምትገኙ ሁሉ ቀደምት የሰው ልጆች መገኛ የሆነችውን ድንቅ ሀገር እንድትጎበኙ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡና በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መስህቦች አሏት፤ ባለፉት 5 ዓመታት በቱሪዝም ዘርፎ በርካታ ኢንቨስትመንት አከናውነናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ድንቅ ሀገር በሆነችው ኢትዮጵያ በርካታ የዓለም ቅርሶች አሉ፤ ይህን መጥቶ መጎብኘት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

የድንቅነሽ ቅሪት የተገኘበት 50ኛ ዓመት ሲከበርም ኢትዮጵያ እንደ ፕሮፌሰር ዮሐንስ ያሉ በዓለም ምርጥ የተባሉ የቅሪተ አካላት ግኝት ያላቸው ተመራማሪዎችን የያዘች ሀገር በመሆኗ በቀጣይም ብዙ ምርምር ይደረጋል ብለዋል።

ድንቅነሽ ድንቅ ናት፤ በድንቅ ሀገር ነው የተገኘችው፤ ከኢትዮጵያ ብትገኝም የዓለም ሀብት ነች ያሉት ዐቢይ ዶ/ር፤ ግኝቱ የሳይንሱን ማኅበረሰብ ብሎም መላውን ዓለም ስለምድራችን እና ስላሳለፈችው የሕይወት መልክ ለማወቅ ያስቻለ መሥራች ሁነት እንደነበር አስረድተዋል።

ግኝቱ ብዙ ጥያቄዎችን የመለሰ ብዙ አዳዲስ ጥያቄዎችን ያነሳሳ ነው፤ በጥያቄዎቹም ለብዙ ምርምሮች መነሻ ሆኖ እስከዛሬ ቀጥሏል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ታሪክ በሰው ልጅ አመጣጥ ላይ ወሳኝ ከሚባሉ 22 ሳይንሳዊ ግኝቶች መካከል 13ቱን ለዓለም ያበረከተች ሀገር መሆኗን ገልጸው፤ እነዚህ ቅሪተ አካላት የሰው ልጅ አመጣጥ ታሪክን በማሳየትና ለሳይንሱ ጉልህ አስተዋጽኦ በማድረግ ወሳኝነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን አንስተዋል።

በሚሊዮኖች ዕድሜ ያስቆጠሩ የድንጋይ ዘመን መሣሪያዎችና ቅሪተ አካላት በኢትዮጵያ መገኘታቸውን አስታውሰው፤ ይህም ኢትዮጵያ የቀደምት ባህላዊ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ባህል መገኛ መሆኗን ያስመሰከረ ነው ብለዋል።

ለዓመታት የተጠናቀሩ ሳይንሳዊ ግኝቶች ኢትዮጵያን ቀደምት የሰው ልጅ መገኛ ከማድረጋቸው በተጨማሪ ኢትዮጵያ የበርካታ ነገሮች መገኛ ሀገር ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የቡና መገኛ፣ የጥንታዊ ሥልጣኔ መነሻ የሆነው የጥቁር ዓባይ መነሻ ሀገር፣ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ 17 የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤትም መሆኗን አብራርተዋል።

በመድረኩ የሉሲ ቅሪተ አካልን በዋና ተመራማሪነት ያገኙት ዶናልድ ጆሐንሰን (ፕ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ወደምድር እንዴት እንደመጣ ለማስረዳት በተደረጉ ሳይንሳዊ ምርምሮች ላይ ወሳኝ አስተዋጽኦ ያበረከተች ሀገር ናት።

በበርካታ የቅሪተ አካላት ግኝቶችና ቅርሶች አማካኝነት የሰው ልጆች ሁሉ መገኛችን ኢትዮጵያ መሆኑ ተረጋግጧል ያሉት ተመራማሪው፤ ባለፈው ታሪካችን የተቆራኘን ለቀጣዩም ለተሻለ ሥራና ምርምር የምንተጋ ነን ሲሉ ተናግረዋል።

በመድረኩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ፣ ኢትዮጵያዊው የቅሪተ አካላትና የሰው ዘር አመጣጥ ተመራማሪ ዮሐንስ ኃይለሥላሴ (ፕ/ር) እንዲሁም የዘርፉ ተመራማሪዎች ተገኝተዋል።

ድንቅነሽ (lucy) በህዳር ወር 1966 ዓ.ም ሐዳር በተባለ ስፍራ በተመራማሪዎች መገኘቷ ይታወቃል።

# መምህራን የሰላም፣...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደሚያስገኝ ተናግረዋል።

“ልጆቻችን ላይ መልካም ዘር በመዝራት የጸናች፣ የበለጸገችና ለትውልድ የምትሸጋገር ኢትዮጵያን እናስቀጥላለን የሚል እምነት አለን” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ መምህራን የሰላም፣ የልማት፣ የመከባበር፣ የመደማመጥና የመወያየት እሳቤ እንዲበዛ ትኩረት አድርገው ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

ትውልድ በቅብብሎሽ ሀገር ማስቀጠል እንዲችል የመምህራን ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ትውልዱ ሀገሩንና ሕዝቡን የሚወድ እንዲሁም የሚያገለግል እንዲሆን እና ከሁሉ በላይ ደግሞ ተረጂ እንዳይሆን በማድረግ ሀገር የማስቀጠል ሥራ የሁሉም ኃላፊነት እንደሆነ ተናግረዋል።

“ልጆች ሙሉ ሰውና ፍሬያማ የሚሆኑት በትምህርት ቤት ውስጥ ነው። ለዚህ ደግሞ የመምህራን ሚና ከፍተኛ ነው” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ማንም ፍሬ አፈራሁ የሚል ቢኖር የመምህራን ውጤት በመሆኑ ለመምህራን የሚሰጠው ክብር ከፍ ያለ መሆን አለበት ብለዋል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ ልዩ የክረምት ብቃት ማሻሻያ ሥልጠናው የትምህርት ቤት ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ አካል ሆኖ በፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በዩኒቨርሲቲዎች በመገኘት የገጽ ለገጽ ሥልጠና በመውሰድ የሙያ ብቃታቸውን የሚያሳድጉበት ነው ብለዋል።፡

በዚህም መሠረት የክረምት መርሀ ግብርን በመጠቀም ለመምህራን የ 120 ሰዓት፣ ለትምህርት ቤት አመራሮች የ60 ሰዓት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እንደሚሰጥ ገልጸው፤ ሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በዚህ መርሀ ግብር እንዲያልፉ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሲሲው ውጤታማነት ሁሉም የድርሻውን ሲወጣ ይገባል!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከፍ ያሉ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎችን እየተጋፈጠችና እየተሻገረች፤ ዕድሎችና ድሎችንም እየፈጠረችና እያስመዘገበች ትገኛለች፡፡ በተለይ ከለውጡ ማግስት ያሉ ስድስት ዓመታት፤ እንደ መንግሥት ብዙ ፈታኝ ሁኔታዎችን እየተጋፈጠ፣ ፈተናዎችን ደግሞ እንደ ዕድል በመጠቀም በፈተና ውስጥ ጣፋጭ ድሎች እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

በዚህም በአንድ በኩል እንደ ሀገር የገጠመውን የግጭትና ጦርነት አዙሪት ዘላቂ እልባት በመስጠት ከችግሮቹ ባሻገር እያሰበ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ እየሠራም ይገኛል፡፡ በሌላው በኩል የዜጎችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ብሎም ሌሎች አስተዳደራዊና የሰላም ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችለውን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ በመንደፍ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

ይሄ የዜጎችን ጥያቄ የመመለስ ጉዞ ደግሞ ሁሉ ነገር ቀና ሆኖለት የሚጓዝ አይደለም፡፡ ይልቁንም በአንድ በኩል የውስጥ የሰላም እና ተያያዥ የአሠራር ችግሮች በእጅጉ አንቀው ይዘውት ነው፡፡ በሌላ በኩል፣ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ከፍ ብላ መራመዷ የማይዋጥላቸው ኃይሎች በተለያየ መልኩ ጫና ሲፈጥሩባት እና የልማቷ እንቅፋት በመሆን ውጫዊ የእጅ ጥምዘዛ ተግባራትን መፈጸማቸው ኢኮኖሚዋ ላይ የሚያሳርፈው ጫና አለ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ሀገራዊም ሆኑ ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎች፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ልታሳካ ካለመችው የብልጽግና መንገድ ፈጽመው ሊያስተጓጉሏት አልቻሉም። ምናልባት ፈተናዎቿን አብዝተው በሚፈለገው ፍጥነት እና ልክ እንዳትጓዝ የቤት ሥራ ይጨምሩባት እንደሆነ እንጂ፤ እስካሁን ባለው ጉዞ ግን መንግሥት ችግሮችን በብልሃትና እውቀት ላይ ተመስርቶ መፍትሔ እየሰጠ፤ የሀገርና ሕዝብን ጥቅም አስጠብቆ በሰጥቶ መቀበልና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ እየተጓዘ ይገኛል፡፡

ከሰሞኑ ይፋ የተደረገው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያም የዚህ የሀገርን እና ሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት ባስጠበቀ መልኩ ከችግሮች ልቆ የመገኘትና የመሻገር ጥበብ አብነት ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ በብዙ ፈተና ውስጥ እያለፈች ከፍ ያለ ድል እያስመዘገበችበት ባለችበት በዚህ ወቅት፤ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ መሸጋገሯ፣ እንደ ሀገር በፈተናዎች ውስጥ ያሉ አቅሞችና ዕድሎችን መለየት ያስቻለ ብቻ ሳይሆን፣ በቀጣይ የሚገጥሙ ፈተናዎችን መሻገሪያ የሚሆን አቅምን መፍጠር የሚያስችላት ነው፡፡

በፖሊሲ ማሻሻያው ማብራሪያ ላይ የተገለጠው እውነትም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በመግለጫው እንደተመላከተው፤ ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ የገባችው በተለያዩ ምዕራፎች ተግባራዊ ስታደርጋቸው በነበሩ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና በመካከለኛው ዘመን የኢንቨስትመንትና የልማት እቅድ ላይ ተመስርታ ነው፡፡

በመሆኑም፣ የፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሙ እንዲሳካ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ጥረቶችና ድርድሮች ከልማት አጋሮች ጋር ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህ መልኩ ከተከናወነው ስምምነት እና ከተገኘው ድጋፍ ባሻገር በቀጣይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የራሱ የሆኑ ዋና ዋና ርምጃዎችና የሚጠበቁ ሀገራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ምክንያቱም በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ በዓለም ባንክ እና በሌሎች ወሳኝ የልማት አጋሮች የሚደገፈው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዲያበረክት የሚጠበቀው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እና ውጤቶች አሉ፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ከማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያው፣ በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት የመዘርጋት ተግባር አንዱ ሥራ ነው፡፡

ይሄ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት የመዘርጋት ተግባር ደግሞ፣ የውጭ ምንዛሬ ግብይት በገበያው አማካኝነት እንዲበየን የማድረግ ሂደት ነው። በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ተመንን ማረጋገጥ ደግሞ በአቅርቦት እና በፍላጎት መካከል ያለውን የውጭ ምንዛሪ መዛባት ለማስተካከል ይረዳል፤ የገቢ እና የወጪ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ዋጋ ከገበያ እውነታዎች ጋር እንዲጣጣም ያስችላል። በክፍያ ሚዛን ላይ ያለውን አለመመጣጠንም ለማስተካከል ይረዳል። ከዚህም ባለፈ ዘላቂና አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ የዋጋ ግሽበት መጠንን ዝቅ ለማድረግ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግና ሀገራዊ የውጭ ምንዛሪ አቅምን ከፍ ለማድረግ ወዘተ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

በዚህ ረገድ የሚጠበቀው ውጤት ይገኝ ዘንድም ይሄንን በትናንትናው እለት ብሔራዊ ባንክ "የውጪ ምንዛሬ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ"ን ወደትግበራ አስገብቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን፣ በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲን ሥርዓትን መዘርጋት፤ የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ፤ የልማት ፋይናንስ ዕድሎች እና የመንግሥት ዕዳ አስተዳደርን ማሻሻልን የመሳሰሉ ጉዳዮችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ምክንያቱም በፖሊሲ ማሻሻያው የሚጠበቁ ውጤቶች ሊገኙም ላይገኙም የሚችሉት በእነዚህ ጉዳዮች ትግበራ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ እያንዳንዳቸው ትግበራዎች የሁሉንም ባለድርሻዎች፣ ዜጎች፣ ምሁራንና ሌሎችም የሚመለከታቸው ተቋማትን ከፍ ያለ ኃላፊነትን የመወጣት ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ ትግበራው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎችን እንዳይጎዳም በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት መጓዘንም ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ለተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲው ውጤታማነት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ሥርዓት ላይ ያደረገው ማሻሻያ

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ሥርዓት ላይ ማሻሻያ ማድረጉን ትናንት ማለዳ ላይ ባወጣው መግለጫ አሳውቋል። ባንኩ ይሄንን ማሻሻያ አስመልክቶ ያወጣው መግለጫ ሙሉ ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፤**

መንግሥት አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምን አስመልክቶ የሰጠውን መግለጫ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በዛሬው ዕለት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን አስታውቋል።

ከዛሬ ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውለው ይህ ማሻሻያ ኢትዮጵያን ተወዳዳሪ ወደሆነና በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራትና በኢኮኖሚ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚያሻሽል ይታመናል። የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው በአዲሱ የውጭ ምንዛሪ መመሪያ መሠረት የሚተገበር ይሆናል።

ይህ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሀ ግብር ላይ የተመሠረተና በቀጣይ ሥራ ላይ ከሚውሉ ሰፊ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ዋና ግቡ ቀጣይነት ያለው፣ መሠረተ ሰፊና ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን ለማረጋገጥ ነው።

### የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው ቁልፍ ይዘት

ከዛሬ ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረገው የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ የሚከተሉትን ዐበይት አዳዲስ የፖሊሲ ለውጦችን ያካትታል፡-

1. የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ወደሚወሰንበት የገበያ ሥርዓት ይሸጋገራል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚና፣ ገበያውን በማረጋጋት ላይ ያተኮረ ይሆናል።
2. የውጭ ምንዛሪን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ቀሪ ሆኗል። በመሆኑም፣ ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት ይችላሉ፤ ይህም ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በእጅጉ ያሻሽላል።
3. ቀደም ሲል በ38 የገቢ ንግድ ሸቀጦች ላይ ተጥሎ የነበረው እግድ ተነሥቷል። ወደ ውጭ የሚደረግ የካፒታል ሂሳብ ፍሰት እንደ በፊቱ የተገደበ ቢሆንም፣ የውጭ ምንዛሪ ገበያው ለገቢ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ነፃ ሆኗል።
4. ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረው 40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ከፍ ብሏል።
5. ቀደም ሲል ባንኮች ለተለያዩ ገቢ ሸቀጦች የሚጠቀሙበት የውጭ ምንዛሪ አሠራርና አደላደል ደንቦች ቀሪ ሆነዋል።
6. አሁን በሥራ ካሉና በባንኮች ከተቋቋሙ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች (Forex Bureaus) በተጨማሪ ባንክ ያልሆኑ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች ይቋቋማሉ። ለእነዚህ ባንክ ላልሆኑ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችም በገበያ ዋጋ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ እንዲገዙና እንዲሸጡ የሥራ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።
7. ሸቀጦችን በፍራንኮ ቫሉታ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ረገድ የተጣሉ ክልከላዎች ለማንሳት በቅርብ ጊዜ የማሻሻያ ደንብ ይወጣል።
8. በውጭ ተቋማት፣ በውጭ ኢንቨስተሮች እና በትውልደ ኢትዮጵያውያን (በዲያስፖራዎች) የተከፈቱ የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን አስተዳደር የሚመለከቱ በርካታ ሕጎች እንዲላሉ ተደርጓል።
9. በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ከውጭ የሚላክላቸውን ሐዋላ፣ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈል ደሞዝን/የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን የሚያስቀምጡባቸውን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች እንዲከፍቱ፣ እንዲሁም እነዚህን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ተጠቅመው የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ ተፈቅዷል።
10. ቀደም ሲል የግል ኩባንያዎች ወይም ባንኮች በሚወስዷቸው የውጭ ብድሮች ላይ ይከፍሉት የነበረው የወለድ ተመን ጣሪያ ተነሥቷል።
11. መመዘኛውን የሚያሟሉ የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) እንዲሳተፉ ተፈቅዷል።
12. በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎች የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት ተሰጥቷቸዋል።
13. ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገራት የሚጓዙ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ መንገደኞች ሊይዙ በሚገባ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ተጥለው የነበሩ የተለያዩ ጥብቅ ደንቦች እንዲላሉ ተደርጓል።

ከላይ በአጭሩ የቀረቡት የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያዎች ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃና ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እያደገ የመጣውን ትስስር ለማጠናከር የሚረዱ ናቸው። ማሻሻያዎቹ የአስር ዓመቱን መሪ ዕቅድና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራምን በመሳሰሉ ቁልፍ ሰነዶች ውስጥ ከሰፈሩት የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ጋር የተናበቡና ወጥነት ያላቸው ናቸው። እነዚህ ሰነዶች ኢኮኖሚው እየተወሳሰበና እያደገ ሲሄድ ሀገሪቱ ቀስ በቀስ በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደምትሸጋገር የሚያወሱ ናቸው። ይህ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ በውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች የዘገየ ቢሆንም፣ አዲስ የበጀት ዓመት መጀመሩና ከዋና ዋና የውጭ የልማት አጋሮች ጋር የተሳካ ውይይትና ድርድር መደረጉ ለውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል።

### የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ለምን?

ከዛሬ ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ምንም ያህል ቀላል ባይሆንም አስፈላጊ ነው። አሁን ያለው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመንና ዝቅተኛ የዋጋ ንረት መኖሩን ለማረጋገጥ የታለመ ቢሆንም፣ በሂደት ግን ለጥቁር ገበያ መስፋፋት፣ ለከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ በከበሩ ማዕድናት ለሚደረግ ሰፊ የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ከባንክ ሥርዓት ውጭ እንዲሆንና ከሀገር እንዲሸሽ አንዱና ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ይህ ሁሉ ከአምራች ዘርፎች ይልቅ ጥቂት ሕገወጦችና ደላሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ሥር የሰደደ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲከሰት አድርጓል። ከዚህም የተነሣ በርካታ የንግድ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ተጎጂ ሆነዋል፤ የወጪ ንግድንና የፋብሪካ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ጥረቶችን ውጤታማነት ሸርሽሮታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ...

ከገጽ 5 የዞረ

**በአንጻሩ፣ በገበያ ወደሚወሰን የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት መሸጋገር በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ያስገኛል፡-**

**አንደኛ፣** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች የተሠማሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ይጠቅማል። ወደ ውጭ የሚላኩ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጫት የመሳሰሉ ሸቀጦችን የሚያመርቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች፣ የቁም እንስሳትና ሥጋ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አርብቶ አደሮችና ነጋዴዎች፣ በወጪ ንግድ ዘርፍ የተሠማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ በማዕድን ፍለጋ ላይ የተሰማሩ በርካታ ዜጎችና አምራቾች፣ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፎች የተሠማሩ በሺህ የሚቆጠሩ ነጋዴዎች፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው/ጓደኞቻቸው የውጭ ምንዛሪ የሚላክላቸው በሚሊዮን የሚገመቱ የሐዋላ ተጠቃሚዎች እንዲሁም ከውጭ ገንዘብ ፈሰስ የሚደረግላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት፣ ከእነዚህም ጋር በሽርክና የሚሠሩና ምርት የሚያቀርቡ ሌሎች አካላት የዚህ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

**ሁለተኛ፣** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በተገቢው መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱንና ለነዋሪዎችና ለአምራች ዘርፎች ጥቅም መዋሉን ለማረጋገጥ ይረዳል። አሁን ያሉ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚደረግ የኮንትሮባንድ ንግድን የሚያበረታቱ፣ ላኪዎችና አስመጪዎች የሸቀጦችን ዋጋ ያለአግባብ ከፍ ወይም ዝቅ እንዲያደርጉ የሚገፉ፣ የካፒታል ሽሽትን የሚያጠናክሩ፣ በጥቅሉ ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትንና በእጅጉ የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያሳጡ ናቸው።

**ሶስተኛ፣** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያበረታታል፤ የማምረት ሥራቸውን እንዲያስፋፉና የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። በኢንዱስትሪና በፍጆታ ዕቃዎች ምርት ዘርፎች የተሠማሩ ተኪ ኢንዱስትሪዎች፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት « ኢትዮጵያ ታምርት» በተሰኘው ዕቅድ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ኢንዱስትሪዎች፣ ከማሻሻያው ተጠቃሚ ይሆናሉ።

**አራተኛ፣** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉን ዘርፍ ለማሳደግና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማዘመን እንዲሁም ኢኮኖሚውን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ለማድረግ የተወሰዱ ሌሎች በርካታ የማሻሻያ እርምጃዎችን የሚደግፍና የሚያጠናክር ይሆናል። ከእነዚህም የማሻሻያ እርምጃዎች መካከል፣ ቀደም ሲል ለግል ዘርፍ/ ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ ዘርፎችን (ለምሳሌ፣ ቴሌኮም፣ ሎጂስቲክስ፣ ባንክ፣ ካፒታል ገበያ፣ ጅምላና ችርቻሮ ንግድ) ክፍት ማድረግ፣ የንግድ ማሳለጫ ሥርዓት ማሻሻል፣ የግል ዘርፍና በመንግሥት ፕሮጀክቶች በአጋርነት ማሳተፍ፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ማቋቋም ወዘተ ይገኙባቸዋል። በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ዘርፎች የተደረጉ ለውጦች ለግሉ ዘርፍና ለኢኮኖሚ ዕድገት አያሌ መልካም ዕድሎችን ቢከፍቱም፣ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ማነቆ ሆነው በመገኘታቸው ማስተካከያ ማድረግ የግድ ሆኗል።

**አምስተኛ፡-** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የንግድ ሥርዓታችንንም ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በአሁኑ ወቅት፣ ኢትዮጵያ ከታላላቅ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎችና በማደግ ላይ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት መካከል የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ሥርዓትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያለባት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ከሕዝብ ብዛት፣ ከሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ከተመጣጣኝና ከተወዳዳሪ ግብዓቶች (የሰው ጉልበት፣ መሬት)፣ ከተጠናከረ የአየር ትራንስፖርትና ከተሻሻለ ሎጂስቲክስ፣ ከኃይል አቅርቦት፣ ከተፈጥሮ ሀብትና ከማዕድናት አኳያ በብዙ መልኩ ለኢንቨስትመንት ምቹና ሳቢ ሀገር ብትሆንም፣ እነዚህ ሁሉ ዕድሎች በአስቸጋሪና ጥብቅ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ምክንያት ውጤታማነታቸው የተጠበቀውን ያህል አልሆነም። ስለዚህ፣ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ለውጭ ኢንቨስተሮች ማነቆ ሆኖ የቆየውን አሠራር ለማስወገድና ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ይጠቅማል።

**ስድስተኛ፡-** የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ በኢኮኖሚው ውስጥ ኢ-መደበኛነትንና ሕገ ወጥነትን ሲያበረታቱ የቆዩ በርካታ የንግድ አሠራሮችን ለማስቀረት ይረዳል። አሁን ያለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማዕቀፍ የውጭ ምንዛሪ በባንኮች በኩል እንዲመጣ የማያበረታታ፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያፈሩ ኩባንያዎች ወይም ግለሰቦች የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ እንዲያሸሹ የሚያደርግ ነው። በውጭ ምንዛሪ የሚካሄድ ኢ- መደበኛ ገበያ እየተስፋፋ በመምጣቱ አብዛኛው የንግድ ማህበረሰብና የሐዋላ ተገልጋዮች በአብዛኛው በጥቁር ገበያ ሲገዙና ሲሸጡ ይስተዋላል። ስለዚህ፣ ዛሬ የተካሄደው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ይህንን የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና እንዲህ ዓይነቱን ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ ይሆናል።

በጥቅሉ፣ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ ርምጃዎችን ለማጠናከር ይረዳል።

**ስፖሊሲው ስኬታማነት ስሚወሰዱ ርምጃዎች ሰፊ በቂ ቅድመ ዝግጅት አድርጓል፡-**

**አንደኛ፣** በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል መንግሥት ከውጭ የሚገቡ የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎም ወስኗል። በዚህ ረገድ፣ መንግሥት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የሚጠቀሙባቸውን ነዳጅን፣ ማዳበሪያን፣ መድኃኒትና የምግብ ዘይትን የመሳሰሉ ከውጭ የሚገቡ የአራት መሠረታዊ ሸቀጦች የዋጋ ጫና በአንድ ጊዜ ወደ ሸማቹ እንዳይተላለፍ ወስኗል።

**ሁለተኛ፣** ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ የዋጋ ንረት ምክንያት የእውነተኛ ገቢያቸው ዋጋ ለተሸረሸረባቸው ወገኖች የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በዋጋ ንረት ምክንያት የደረሰውንና ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማርገብ ሲባል ያለውን የገንዘብ ምንጭ በመጠቀምና የመንግሥትን የበጀት ጉድለት በማያባብስ መልኩ ለመንግሥት ሠራተኞች የኑሮ ውድነት መደጎሚያ ደሞዝ ለመጨመር ታስቧል። እንዲሁም፣ በከተማም ሆነ በገጠር ለሚገኙ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚደረገው የሴፍቲኔት ርዳታ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል። የእነዚህ ርምጃዎች ዝርዝር አፈጻጸም በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የሚገለጽ ይሆናል።

**ሶስተኛ፣** የመንግሥትን የማህበራዊ ወጪ ለመደገፍና ለውጭ ዕዳ ክፍያ የሚውለው ከፍተኛ የብር ወጪ ሌሎች ወጪዎችን በማይሻማ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ የውጭ ዕዳ ማቅለያ ርዳታ ተገኝቷል። ይህን መሰል ርዳታ ቀደም ብሎ መገኘቱ መንግሥት ለማህበራዊና ድህነት ተኮር ወጪዎች የሚያውለው የሀብት አመዳደብ እንዳይስተጓጎልና በቀጣይ ዓመታትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይረዳዋል።

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የመፍትሔ ርምጃዎች ባሻገር፣ ወደ አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት የሚደረገውን ሽግግር ለማሳለጥና በገንዘብና በፊስካል ፖሊሲዎች መካከል ቅንጅት መኖሩን ለማረጋገጥ የብሔራዊ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር ትብብር ተጠናክሮ ይቀጥላል። ለምሳሌ፡-

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረትን የሚያረግብባቸው አዳዲስ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ውለዋል። ባንኩ ካለፈው ዓመት ጀምሮ በባንክ ብድር ዕድገት ላይ ካስቀመጠው ገደብ ሌላ፣ የገንዘብ ዕድገት የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ሥርዓቱን እንዳይሸረሽር ለመከላከልና የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የሚረዳ በወለድ ተመን ላይ የተመሠረተ አዲሱን የገንዘብ ፖሊሲ በቅርቡ ተግባራዊ አድርጓል።

የገንዘብ ሚኒስቴር ጠንካራ የገቢ መሠረት ለመጣልና የዋጋ ንረትን የሚያባብሱ (ለምሳሌ ከብሔራዊ ባንክ የሚወሰድ ቀጥታ ብድርን የመሳሰሉ) የመበደሪያ ስልቶችን ሳይጠቀም የመንግሥት ወጪን ለማሳደግ የሚያስችሉ ርምጃዎች ሥራ ላይ ማዋል በመጨረሻም፣ የሽግግር ወቅት ወጪዎችንና የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ የሚያስከትላቸውን ጫናዎች ለመቀነስ የሚረዳ 10.7 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ትልቅ የገንዘብ ድጋፍ ከውጭ አጋሮች ተገኝቷል። ይህ የገንዘብ ድጋፍ ከዓለም የገንዘብ ድርጅት፣ ከዓለም ባንክና ከአበዳሪዎች የሚገኘውን ይጨምራል።

ነገር ግን፣ በሁለትዮሽ የማዕከላዊ ባንክ ተቀማጭ (central bank deposits) እና በከረንሲ, ልውውጥ (currency swap) መልክ የሚመጣውን 2.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሁም ከዓለም ባንክ፣ ከዓለም አቀፍ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC) እና ከሌሎች ባለብዙ ወገኖች (multilaterals) ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀውንና በሂደት ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ይፋ የሚደረገውን ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ አያካትትም። ይህ የዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የሚለግሱት ልዩ የገንዘብ ርዳታ የመንግሥትን የሪፎርም ሥራዎችን ጥንካሬ ያገናዘበና በአፍሪካ አህጉር ትልቁ ከሚባሉት የገንዘብ ርዳታዎች አንዱ ነው።

በቀጣይ የሚወሰዱ ርምጃዎች የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ሥራ ላይ መዋል፣ ከሌሎች አጋዥ ማክሮ ርምጃዎች ጋር ተዳምሮ፣ ኢትዮጵያ ዕድገቷንና የወደፊት ብልጽግናዋን እንድታፋጥን ዓይነተኛ ዕድል ይሰጣታል። ቁልፍ የሆኑ መሰናክሎችንና አደናቃፊ እክሎችን በማስወገድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመጪዎቹ ዓመታት ትልቅ እመርታ እንደሚያሳይ ይጠበቃል። በዓለም የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ትንታኔ መሠረት፣ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የማሻሻያ ርምጃዎች ዕድገትን ለማፋጠን፣ የዋጋ ንረትን ለማርገብ፣ የፊስካል አቅምን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግድንና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

እንዲሁም በዚሁ ትንበያ መሠረት፣ በማሻሻያ ርምጃዎቹ ምክንያት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በ8 በመቶ ያህል ያድጋል፤ የዋጋ ንረት ወደ 10 በመቶ የተጠጋ ይሆናል፤ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ ይደርሳል፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ ይላል፤ የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ያድጋል፤ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ 8 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ይላል፤ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ከ10 ቢሊዮን ዶላር (የ3.3 ወራት የገቢ ሸቀጦችን ወጪ ለመሸፈን የሚበቃ) በላይ ይሆናል። እነዚህ ትንበያዎች በቀጣይ ዓመታት ከላይ በተጠቀሱት ማሻሻያዎች ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የኢኮኖሚ ሽግግር ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸው።

በሚቀጥሉት ሳምንታትና ወራት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታን የማረጋገጥ ቁልፍ ኃላፊነቱን ከመወጣት ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያውን ስኬታማና ውጤታማ በማድረግ ላይ የሚያተኩር ይሆናል። እነዚህንም ተግባራት ለማከናወን ባንኩ በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ስለማሻሻያው ተፈላጊውን መረጃ ለሕዝቡና ለገበያ ተዋናዮች በመግለጫ መልክ ይሰጣል።

**በዚሁ መሠረት የሚሰጡ ገለጻዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-**

በገበያ ላይ ተመሥርቶ የሚዘጋጀውን የውጭ ምንዛሪ ተመን አመልካች ዕለታዊ መረጃ መስጠት፤ እንደ አስፈላጊነቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለሚያካሂደው የውጭ ምንዛሪ ጨረታ (አጠቃላይ የአቅርቦት መጠኑንና የምንዛሪ ተመኑን ያካተተ) መረጃ መስጠት፤ ስለ ገበያው ውሎ፣ ስለ ሐሰተኛ መረጃዎችና ሌሎች አሉባልታዎች እንዲሁም ምላሽ ለሚያስፈልጋቸው ዓበይት ጉዳዮች መረጃና ማብራሪያ መስጠት፣ ስለ አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያ ከባንኮች፣ ከደንበኞችና ከሰፊው ሕዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠት።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚቀጥሉት ወራት ለቁጥጥርና ለክትትል ሥራዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል። አብዛኞቹ የውጭ ምንዛሪ ሥራዎች በውክልና ወደ ባንኮች በመተላለፋቸው፣ ባንኮቹ አዲሱን የውጭ ምንዛሪ መመሪያ በጥብቅ ስለመተግበራቸው፣ በተለይም የውጭ ምንዛሪ ለሕጋዊ ግብይቶች ብቻ መዋሉን ስለማረጋገጣቸው ብሔራዊ ባንኩ ጥብቅ ክትትል ያደርጋል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ባንኮች ከወጪ ንግድ ገቢ ስለሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ክፍፍል (export retention) የወጡ ደንቦችን፣ ስለባንኮች ዕለታዊ የውጭ ምንዛሪ ሀብትና ዕዳ የተቀመጡ ገደቦችን (dally net open position) እንዲሁም ስለ ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር (Anti-Money Laundering) ቁጥጥር የተዘረጉ አሠራሮችን በጥብቅ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

በውጭ ምንዛሪ ተመን ወይም በአገልግሎት ክፍያ ረገድ የማጭበርበር ድርጊት በጥብቅ የተከለከለ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ዘዴዎችን፣ በተለይም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና እንደ አስፈላጊነቱ ከፋይናንስ ደህንነትና ሌሎች ሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር እነዚህን የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች ያከናውናል። ሕግን በሚተላለፉት ላይም አስተማሪ ርምጃ ይወሰዳል።

በመጨረሻም፣ ኢትዮጵያ ፈጣን፣ ክፍትና ተወዳዳሪ ከሆኑ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎች መካከል አንዷ ለመሆን በጀመረችው የለውጥ ጉዞ የሀገራችን ቁልፍ የውጭ ምንዛሪ ተዋናዮችና የባንኩ ማህበረሰብ እንዲሁም ሰፊው ህብረተሰብ ለኢትዮጵያና ለመላ ሕዝቦቿ ጥቅም ሲሉ ለዚህ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ስኬታማነት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## አካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞችን መመገብ የሚችል ሮቦት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ቴክኖሎጂ የሰውን ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወት ቀላል ያደርጋል፤ ይህን በመጠቀም ሰዎች ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ መቆጠብ ችለዋል፤ ከእንግልት ድነዋል፤ ምርታማ ሆነዋል፤ ወዘተ.።

ቴክኖሎጂን ብዙኃኑን የማከለና አካታች እንዲሆን በማድረግም የበለጠ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል። በተለይ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል። በዘርፉ የፈጠራ ሃሳብ መማነጨት የሚችሉና ፍላጎቱ ያላቸው የፈጠራ ባለሙያዎች የህብረተሰቡን ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ እንደዚህ ዓይነት ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር ላይ መሥራትም ይጠበቅባቸዋል።

የፈጠራ ሃሳብ ለችግሮች መፍትሔ ለማፈላለግ በሚሰሩ ሰዎች የሚመነጭ እንደመሆኑ በቅርበት የሚታየውን የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ሆነው፣ ጥናት ላይ የተመረኮዙ ችግሮችን ሊፍቱ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎች እንደሚሰሩም ይታወቃል። በጥናት ላይ የተደገፉ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨት ከሚታወቁት መካከል የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ይጠቀሳሉ።

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የህብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት ጉልህ ድርሻ አላቸው። ዘንድሮም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት በርካታ ችግር ፈቺ ፈጠራዎች ተሰርተው በ14ተኛው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት አውደ ርዕይ ላይ ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል የጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰልጣኙ ወጣት ዳግም ጋርጠው የሰራት አካል ጉዳተኞችን፣ አቅመ ደካሞችንና ሕፃናትን መመገብ የምትችል ሮቦት ትጠቀሳለች።

ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች ትልቁ ችግር የሆነ ራስን ችሎ ከቦታ ወደ መንቀሳቀስ አለመቻል ብቻ አይደለም፤ ምግብ በራሳቸው መመገብ አለመቻላቸውም ይነሳል። ይህ ችግር የሚመግባቸው ሌላ ሰው እንዲኖር የግድ ሲልም ይስተዋላል። ራሳቸውን ችለው እንዲመገቡ የሚያስችላቸው ሁኔታ ቢኖር ግን ሰው ላያስፈልግ ይችላል። ወጣት ዳግም አካል ጉዳተኞችን በመመገብ ይህን ችግር መፍታት የምትችል ሮቦት ነው የሰራው።

ከአንገት በታች ያለው የሰውነት ክፍላቸው የማይሰራ ወይም ፓራላይዝድ የሆኑ እንዳሉ ሁሉ፤ የነርቭ ችግር ያለባቸው፣ እጃቸው የሚንቀጠቀጥባቸው አካል ጉዳተኞችም አሉ። በተፈጥሮ ከአካል ጉዳት ጋር የሚወለዱ ሕፃናትም የችግሩ ሰለባ ናቸው። በተለይ ሕፃናቱ የሰውን ርዳታ በእጅጉ የሚፈልጉ ከመሆናቸውም በላይ ያለ ሰው ድጋፍ ምንም ማድረግ ስለማይችሉ ወላጆቻቸው በተለይም እናቶቻቸው ሌላ ሥራ መሥራት ትተው እድሜ ዘመናቸውን ሙሉ እነሱን ሲንከባከቡ ለማሳለፍ ሲገደዱ ይታያሉ።

በተቋማት ደረጃም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ሰብስበው የሚንከባከቡና የሚረዱ እንደ መቄዶንያ ዓይነት አረጋዊያን መንከባከቢያ ማዕከላት አሉ። እነዚህን ሁሉ የተመለከተው ወጣት ዳግም የእነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ምን ባደርግ የተሻለ ነገር መሥራት እችል ይሆን? ብሎ በጥልቀት በማሰብ ጥናት አድርጎበት ሁሉንም አካታች የሆነ የፈጠራ ሥራ መሥራቱን ይናገራል።

ወጣት ዳግም እንደሚለው፤ ሮቦቷ ፕሮግራም ተደርጋ በቻርጀር ብቻ መንቀሳቀስ የምትችል ተደርጋ ነው የተሰራችው። የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ለማገልገል ታስባ የተሰራች በመሆኗም ጉልበት፣ ጊዜና ወጪን ትቆጥባለች። በቀላሉ በአነስተኛ ዋጋ እንድትገኝ ተደርጋ የተሰራች ከመሆኗ በተጨማሪ ብዙ ሰው ሊጠቀምባት እንድትችል ተደርጋ ተሰርታለች። «ሮቦቷን ለመሥራት ትምህርት ቤት የሚማርባቸውን ቁሳቁስ ተጠቅሜለሁ። መቆጣጠሪያ፣ ሞተርና በዋጋቸው ቀላል የሆነ ቁሳቁስ ሥራ ላይ አውያለሁ» ይላል።

ዳግም አካል ጉዳተኞችን መመገብ የምትችል ሮቦት ለመሥራት ሃሳቡን አመንጭቶ ከጠነሰሰ በኋላ



ወጣት ዳግም ጋርጠው

በችግሩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችንም ተመልክቷል። ጥናቶቹ ችግሩ ምን ያህል ሰፊ እንደሆነ ጠቁመውታል። ጊዜ ሳያጠፉ በፍጥነት ወደ መፍትሔ ፍለጋ መግባት እንዳለበትም አስገንዝበውታል።

በቅርቡ የተካሄዱ ጥናቶችን ዋቢ አድርጎ ሲያብራራ እንደገለጸውም፤ በዓለም ላይ በዚህ ችግር ውስጥ የሚገኙ ወደ አንድ ቢሊዮን የሚጠጉ አካል ጉዳተኞች አሉ። በኢትዮጵያ ደግሞ 19 ሚሊዮን የሚደርሱ አካል ጉዳተኞች ይገኛሉ።

እነዚህን አካል ጉዳተኞች የማገዙ ሥራ የዘመኑ ቴክኖሎጂ በሚፈቅድው ልክ መሥራትን ይጠይቃል። በተለይ በዚህ የሰው ሠራሽ አስተውሎት በተራቀቀበት ዘመን እነሱን ለማገዝ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም መሥራት ይገባል። ወጣት ዳግምም በዚህ ሃሳብ መነሻነት በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚታገዝ ሮቦት ሰርቷል።

ወጣት ዳግም እንደሚለው፤ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በራሳቸው መመገብ ቢችሉም እንኳን በመሀል እየተመገቡ መሆናቸውን ረስተው ጀምረው የሚተውባቸው አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ምግቡን የጎረሱ እየመሰላቸው የሚደፉበት ሁኔታም ይኖራል። በዚህ ጊዜ ምግብ የበሉ ይመስላቸውና ተደፍቶ ሲያልቅ ተበሳጭተው እስከነአካቴው የምግብ ፍላጎታቸው እንዲጠፋ ይሆናል። ይቺ ሮቦት ግን እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ትችላለች።

ሮቦቷ ለተጠቃሚዎች የምትሰጠው አገልግሎት ምግብ መመገብ ብቻ ሳይሆን መጠጥ የማጠጣት አገልግሎትም ትሰጣለች። ይሁን እንጂ አሁን ላይ ሁሉም የምግብ ዓይነቶች ለመመገብ አትችልም። ቀለል ያሉ ምግቦችን ነው መመገብ የምትችለው።

ለምሳሌ እንደ መኮሮኒ፣ ሩዝ እና ፍርፍር እና ሾርባዎች ያሉ በተለይ በማንኪያ መበላት የሚችሉ የምግብ ዓይነቶችን መመገብ ትችላለች። በአንድ ጊዜ ሁለት ዓይነት ምግቦችንም ትመግባለች። በመጠጥም በኩል ውሃ፣ ጁስ፣ ወተትና መሰል ሌሎች የመጠጥ ዓይነቶች በመቀያየር ታጠጣለች።

ሮቦቷ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ፕሮግራም የተደረገች ሲሆን ለመቆጣጠር የሚያስችለው ማይክሮ ኮንትሮለርና እንቅስቃሴ የምታደርግባቸው ሞተሮች የተገጠሙላትም ናት፤ ፕሮግራሙ አንድ ጊዜ የተጫነ በመሆኑ በቀላሉ ለማዘዝም ሆነ ለመቆጣጠር ይቻላል።

ፕሮግራምም ሲጫን አንድ ሰው በአንድ ጊዜ መመገብ የሚችለው የማንኪያ መጠንና በምን ያህል ፍጥነት መመገብ ይችላል? የሚሉት ይቆጠሩለታል። ይህ ከተቆጠረ በኋላ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ መመገብ የሚችለው መጠን በአማካይ ይቀመጣል። ለአንድ ሰው የሚመጠነው የአንድ ጊዜ ምግብም በፓኬጅ መልኩ ለሮቦቷ ይሞላል። አገልግሎቱን ለመስጠት ሲፈለግ ሮቦቷ አገልግሎቱን እንድትጀምር የሚያደርግ አንድ ሰው ያስፈልጋል። ሰውዬው አገልግሎቱን ካስጀመረለት በኋላ ሮቦቷ ራሷን ችላ ምግቡን መግባ መቆም ባለበት ሰዓት ስለምታቆም በዚያው የምገባ አገልግሎቱ ይጠናቀቃል።

ሮቦቷ አካል ጉዳተኞችንና አቅመ ደካሞችን ለመመገብ የተዘጋጀች እንደመሆኑ እነሱ የሚመገቡበትን የጊዜ ልዩነት በደንብ ከግንዛቤ በማስገባት ጥናት ተደርጎ ያንን የጊዜ ገደብ እንዲጠብቅ ተደርጎ ፕሮግራም የተደረገ መሆኑን የሚገልጸው ወጣት ዳግም፤ ይሁንና ፍጥነቱን መጨመርና መቀነስ ከተፈለገ በተጠቃሚ ፍላጎት እንዲሆን ይደረጋል።

«ፍጥነት ለመቀነስ የተቀመጠውን የጊዜ ልዩነት ስንቀንስ ሮቦቷም በዚያም ልክ የፍጥነት መጠኗን ትቀንሳለች ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ፍጥነት በመጨመር ቶሎ ቶሎ መመገብ የሚፈልግ ተጠቃሚ ቢያጋጥምም እንደዚሁ የተቀመጠውን የሰዓት ልዩነት በመጨመር ፍጥነት እንድትጨምር ማድረግ እንችላለን» ይላል።

እንደ እሱ ማብራሪያ፤ ሮቦቷ በዚህ መልኩ ተሰርታ ተግባር ላይ ትዋል እንጂ ያልተሟሉ ጥቃቅን ነገሮች አሏት። ለምሳሌ ውጫዊ ክፍሏ ቢቀየርና ሴንሰሮች ቢጨመሩላት የተሻለ አገልግሎት መስጠት ትችላለች። ምክንያቱም ሁሉም አካል ጉዳተኛም ሆነ አቅመ ደካማ ያለበት ችግር አንድ ዓይነት ስላልሆነ ይህን በማድረግ ሁሉንም እንደየሁኔታቸው ለማስተናገድ ይቻላል። ለአብነት ዓይነስውራን ሆነው መመገብ የማይችሉን ብንወስድ በሮቦቷ አማካኝነት እንዲመገቡ ሲደረግ ተመጋቢዎቹ በሴንሰሮች አማካኝነት መመገብ እንዲችሉ ብዙ ሴንሰሮች ስለሚያስፈልግ ይህን በማካተት መሻሻል ይቻላል።

እነዚህን ሥራዎች መሥራት ቀላል ቢሆንም የፋይናንስ አቅም እንደሚጠይቁ ጠቅሶ፤ በቀጣይ መሻሻል ያለባቸውን በማሻሻል የተሻለ ለመሥራት ጥረት እንደሚያደርግ ይገልጻል። «ሮቦት ለመሥሪያ የሚያገለግሉ ሮቦቲክስ ቁሳቁስ በሀገር ውስጥ ማግኘት አስቸጋሪ ነው» የሚለው ወጣት ዳግም፤ ሮቦቷን ለመሥራት ያጋጠሙት ተግዳሮቶች እንደ ሀገር ያሉና የሚታዩ ችግሮች መሆናቸውን ያነሳል። ለሮቦቱ መሥሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁስ በሀገር ውስጥ የሚገኙባቸው ቦታዎች ውስን ከመሆናቸውም በላይ የፋይናንስ አቅምን የሚጠይቁ መሆናቸውም ይገልጻል።

«እኔ ይቺን ሮቦት ስሰራ ለሮቦቱ መሥሪያ የሚውሉ ቁሳቁስን ድጋፍ ያደረገልኝ ኮሌጁ ነው። የቁሳቁሱ አለመሟላት ለሥራዬ እንቅፋት ሆኖብኛል፤ ሥራው እንዲዘገይ ምክንያትም ሆኗል። ኮሌጁ ድጋፍ ባይደርግልኝ ኖሮ በራሴ ለመሥራት በፋይናንስ አቅም ሳቢያ እቸገር ነበር» ይላል።

በዚህም የተነሳ የሮቦቷ ሃሳብ እንደመነጨለት በፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ በማሰብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሰራች መሆኗን ጠቅሶ፣ መጠነኛ ማሻሻያ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታል። አሁን ላይ ያለው የሮቦቷ ሥራ ሙሉ ባይሆንም ከፕሮቶታይፕ ደረጃ ከፍ ያለና ባለበት ሁኔታም አገልግሎት መስጠት የምትችል ናት። ሮቦቷ አገልግሎቱን መስጠት እንደምትችል ለማረጋገጥ በተደረገላት ፈተሻ አገልግሎት ላይ መዋል እንደምትችል ማረጋገጥ ተችሏል ሲል ያስረዳል።

ሮቦቷን በማሻሻል ከዚህ በበለጠ መልኩ ለመሥራት የተለያዩ ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ ጠቅሶ፤ ለአብነትም የሮቦቷ ውጫዊ አካል ጥንካሬ እንዲኖረው ማሻሻያ ተደርጎ አሁን ከተሰራበት ውጭ በሆነ በሌላ ቁሳቁስ እንድትስራ ቢደረግ ጥንካሬ ያለው ሮቦት መሥራት እንደሚቻል ነው ያስገነዘበው።

አሁንም ሌሎች የፈጠራ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ጠቅሶ፣ በቀጣይም እነዚህን ሥራዎች በማጠናቀቅ ጥቅም ላይ በማዋል ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ጥረት እንደሚያደርግ ይገልጻል። ኢንዱስትሪያል ኤሌክትሪካል ኮንትሮለር ቴክኖሎጂ የተሰኘ ትምህርት እየተማረ መሆኑን ጠቅሶ፤ ትምህርቱም በአብዛኛው በኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ ዙሪያ ትኩረት እንደሚያደርግ ያስረዳል። በዚህ ዘርፍ የሚጠበቅበትን ለማበርከት የበኩሉን እንደሚሰራ ያመለክታል።

አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች በሰው ኃይል እንደሚሰሩ ጠቅሶ፣ ብዙ የሰው ኃይል የሚጠቀሙና ጊዜን የሚወስዱ እንዲሁም አደጋም ሊያስከትሉ የሚችሉ ሥራዎች የሚሰሩባቸው እንደሆኑ ይጠቁማል። ይህም በቴክኖሎጂ ቢቀየር ጉልበት፣ ጊዜን፣ ወጪንና ብዙ ነገሮች ሊቆጥብ እንደሚችል ይናገራል። እንደዚህ ዓይነት አሠራሮች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል።

እንደ ወጣት ዳግም ገለፃ፤ እሱ ወደ ፈጠራ ሥራዎች የገባው ገና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን እየተማረ ባለበት ወቅት ነበር፤ በትምህርት ቤት ቆይታውም የፈጠራ ሥራዎችን ሰርቶ ለውድድር በማብቃት አሸናፊ ሆኖም ያውቃል። በዚህም የምስክር ወረቀት፣ የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማቶች አግኝቷል። ከፈጠራ ሥራዎቹ መካከል የከተማ ማጽጃ፣ አውቶማቲክ ቡና ማፊያ ማሽንና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

ወጣት ዳግም የግሉ የፈጠራ ሥራ የሆነችው ይቺ ሮቦት በዘንድሮው 14ተኛው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ላይ አንደኛ መውጣቷንም ጠቅሶ፣ በዚህም የሰርተፊኬትና የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶለታል። ይህም ለቀጣይ ሥራ ሞራልና ማበረታታ እንደፈጠረለት ይናገራል።

በተለይ በፈጠራ ሥራዎች የሚሰሩ ወጣቶች ማወቅና መገንዘብ ያለባቸው የፈጠራ ሥራ ብዙ ተግዳሮት እንዳለበት ወጣት ዳግም አመልክቷል። የፈጠራ ክህሎቱ፣ እውቀቱና የመሥራት አቅሙ ያለው ሰው፣ በፋይናንስ እጦት የሚከሰቱ ተግዳሮቶችንም በአሸናፊነት ለማለፍ ጥረት ማድረግ እንዳለበትም አስገንዝቧል። የፈጠራ ሥራዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ዝቅተኛ ነው ሲል ጠቅሶ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ በመሥራት የፈለጉትን አላማ ማሳካት እንደሚቻል በማመን ጥረት ማድረግ እንደሚገባም ነው ያስገነዘበው።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ትሩፋቶች

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ይፋ አድርጓል። አዲሱ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትና ዘላቂነትን በሚደገፍ ዘመናዊና ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማእቀፍ ለመመሥረት የሚያስችል ነው። ፈጠራን የሚያበረታታና ምቹ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ከባቢና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ ይሆናል ተብሎ ታምኖበታል። የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት አቅምን የሚያጠናክርና ጥራት ያለው አገልግሎትን በብቃት ለማቅረብ የመንግሥትን አቅም ማሳደጊያ እንደሚሆንም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያወጣው መግለጫ ያስቀምጣል።

ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን አስታውቋል። የብሄራዊ ባንክ ገዢ አቶ ማሞ ምህረቱ ማሻሻያውን አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ማሻሻያው ኢትዮጵያን ተወዳዳሪ ወደሆነና በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራትና በኢኮኖሚ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚያሻሽል አስቀምጠዋል።

ይህ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሀ ግብር ላይ የተመሠረተና በቀጣይ ሥራ ላይ ከሚውሉ ሰፊ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ዋና ግቡም ቀጣይነት ያለው፣ መሠረተ ሰፊና ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን ማረጋገጥ ነው። ማሻሻያው ካካተታቸው ዐበይት አዳዲስ ፖሊሲዎች መካከልም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ወደሚወስንበት የገበያ ሥርዓት ይሸጋገራል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚና፣ ገበያውን በማረጋጋት ላይ ያተኮረ ይሆናል። የውጭ ምንዛሪን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ቀሪ አድርጎታል። በመሆኑም፣ ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት ይችላሉ ይህም ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በእጅጉ የሚያሻሽለው ይሆናል።

ቀደም ሲል በ38 የገቢ ንግድ ሸቀጦች ላይ ተጥሎ የነበረው እግድ ተነስቷል። ወደ ውጭ የሚደረግ የካፒታል ሂሳብ ፍሰት እንደ በፊቱ የተገደበ ቢሆንም፣ የውጭ ምንዛሪ ገበያው ለገቢ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ነጻ ሆኗል። በተጨማሪ ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረው 40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ከፍ ብሏል። ቀደም ሲል ባንኮች ለተለያዩ ገቢ ሸቀጦች የሚጠቀሙበት የውጭ ምንዛሪ አሠራርና አደላደል ደንቦች ቀሪ ሆነዋል።

አሁን በሥራ ካሉና በባንኮች ከተቋቋሙ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች በተጨማሪ ባንክ ያልሆኑ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች ይቋቋማሉ። ለእነዚህ ባንክ ላልሆኑ የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችም በገበያ ዋጋ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ እንዲገዙና እንዲሸጡ የሥራ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። ሸቀጦችን በፍራንኮ ቫሉታ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ረገድ የተጣሉ ክልከላዎች ለማንሳት በቅርብ ጊዜ የማሻሻያ ደንብ ይወጣል። በውጭ ተቋማት፣ በውጭ ኢንቨስተሮች እና በትውልደ ኢትዮጵያውያን የተከፈቱ የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን አስተዳደር የሚመለከቱ በርካታ ሕጎች እንዲላሉ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ከውጭ የሚላክላቸውን ሐዋላ፣ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈል ደሞዝን/የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን የሚያስቀምጡባቸውን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች እንዲከፍቱ፣ እንዲሁም እነዚህን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ተጠቅመው የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ ተፈቅዷል። ቀደም ሲል የግል ኩባንያዎች ወይም ባንኮች በሚወስዷቸው የውጭ ብድሮች ላይ ይከፍሉት የነበረው የወለድ ተመን ጣሪያ ተነስቷል።

መመዘኛውን የሚያሟሉ የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ እንዲሳተፉ ተፈቅዷል። በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎች የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት ተሰጥቷቸዋል። ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገራት የሚጓዙ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ መንገደኞች ሊይዙ በሚገባ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ተጥለው የነበሩ የተለያዩ ጥብቅ ደንቦች እንዲላሉ ተደርጓል።

ከላይ በአጭሩ የቀረቡት የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያዎች ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃና ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እና እያደገ የመጣውን ትስስር ለማጠናከር የሚረዱ ናቸው። እንዲሁም ማሻሻያዎቹ የአስር ዓመቱን መሪ ዕቅድና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራምን በመሳሰሉ ቁልፍ ሰነዶች ውስጥ ከሰፈሩት የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ጋር የተናበቡና ወጥነት ያላቸው ናቸው።



እነዚህ ሰነዶች ኢኮኖሚው እየተወሳሰበና እያደገ ሲሄድ ሀገሪቱ ቀስ በቀስ በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደምትሸጋገር የሚያወሱ ናቸው። ይህ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ በውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች የዘገየ ቢሆንም፣ አዲስ የበጀት ዓመት መጀመሩና ከዋና ዋና የውጭ የልማት አጋሮች ጋር የተሳካ ውይይትና ድርድር መደረጉ ለውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ መልካም አጋጣሚ ፈጥረዋል።

አሁን ያለው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ ተመንና ዝቅተኛ የዋጋ ንረት መኖሩን ለማረጋገጥ የታለመ ቢሆንም፣ በሂደት ግን ለጥቁር ገበያ መስፋፋት፣ ለከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ በከበሩ ማዕድናት ለሚደረግ ሰፊ የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ከባንክ ሥርዓት ውጭ እንዲሆንና ከሀገር እንዲሸሽ አንዱና ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ይህ ሁሉ ከአምራች ዘርፎች ይልቅ ጥቂት ሕገወጦችና ደላሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑና ሥር የሰደደ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዲከሰት አድርጓል። በዚህም የተነሣ በርካታ የንግድ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ተጎጂ ሆነዋል፤ የወጪ ንግድንና የፋብሪካ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ጥረቶችን ውጤታማነትም ሸርሽሮታል።

በአንጻሩ፣ በገበያ ወደሚወሰን የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት መሸጋገር በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ያስገኛል። ከእነዚህም መካከል የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች የተሠማሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ይጠቅማል። ወደ ውጭ የሚላኩ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጫት የመሳሰሉ ሸቀጦችን የሚያመርቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች፣ የቁም እንስሳትና ሥጋ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አርብቶ አደሮችና ነጋዴዎች፣ በወጪ ንግድ ዘርፍ የተሠማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ በማዕድን ፍለጋ ላይ የተሰማሩ በርካታ ዜጎችና አምራቾች፣ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፎች የተሠማሩ በሺህ የሚቆጠሩ ነጋዴዎች፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው/ጓደኞቻቸው የውጭ ምንዛሪ የሚላክላቸው በሚሊዮን የሚገመቱ የሐዋላ ተጠቃሚዎች እንዲሁም ከውጭ ገንዘብ ፈስስ የሚደረግላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት፣ ከእነዚህም ጋር በሽርክና የሚሠሩና ምርት የሚያቀርቡ ሌሎች አካላት የዚህ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በተገቢው መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱንና ለነዋሪዎችና ለአምራች ዘርፎች ጥቅም መዋሉን ለማረጋገጥ ይረዳል። ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያበረታታል፤ የማምረት ሥራቸውን እንዲያስፋፉና የገበያ ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። በኢንዱስትሪና በፍጆታ ዕቃዎች ምርት ዘርፎች የተሠማሩ ተኪ ኢንዱስትሪዎች፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት «ኢትዮጵያ ታምርት» በተሰኘው ዕቅድ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ኢንዱስትሪዎች፣ ከማሻሻያው ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግሉን ዘርፍ ለማሳደግና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማዘመን እንዲሁም ኢኮኖሚውን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ለማድረግ የተወሰዱ ሌሎች በርካታ የማሻሻያ ርምጃዎችን የሚደግፍና የሚያጠናክር ይሆናል። ከእነዚህም የማሻሻያ ርምጃዎች መካከል፣ ቀደም ሲል ለግል ዘርፍ/ ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ ዘርፎችን ክፍት ማድረግ፣ የንግድ ማሳለጫ ሥርዓት ማሻሻል፣ የግል ዘርፍና በመንግሥት ፕሮጀክቶች በአጋርነት ማሳተፍ፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ማቋቋም ወዘተ ይገኙባቸዋል።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ዘርፎች የተደረጉ ለውጦች ለግሉ ዘርፍና ለኢኮኖሚ ዕድገት አያሌ መልካም ዕድሎችን ቢከፍቱም፣ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲዎች ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ማነቆ ሆነው በመገኘታቸው ማስተካከያ ማድረግ የግድ ሆኗል።

በተጨማሪ የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የንግድ ሥርዓታችንንም ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በአሁኑ ወቅት፣ ኢትዮጵያ ከታላላቅ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎችና በማደግ ላይ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት መካከል የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ሥርዓትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያለባት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ከሕዝብ ብዛት፣ ከሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ከተመጣጣኝና ከተወዳዳሪ ግብአቶች (የሰው ጉልበት፣ መሬት)፣ ከተጠናከረ የአየር ትራንስፖርትና ከተሻሻለ ሎጂስቲክስ፣ ከኃይል አቅርቦት፣ ከተፈጥሮ ሀብትና ከማዕድናት አኳያ በብዙ መልኩ ለኢንቨስትመንት ምቹና ሳቢ ሀገር ናት ።

ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ዕድሎች በአስቸጋሪና ጥብቅ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ምክንያት ውጤታማነታቸው የተጠበቀውን ያህል አልሆነም። ስለዚህ፣ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ለውጭ ኢንቨስተሮች ማነቆ ሆኖ የቆየውን አሠራር ለማስወገድና ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ይጠቅማል።

በኢኮኖሚው ውስጥ ኢ-መደበኛነትንና ሕገ ወጥነትን ሲያበረታቱ የቆዩ በርካታ የንግድ አሠራሮችን ለማስቀረት ይረዳል። አሁን ያለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማዕቀፍ የውጭ ምንዛሪ በባንኮች በኩል እንዲመጣ የማያበረታታ፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያፈሩ ኩባንያዎች ወይም ግለሰቦች የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ እንዲያሸሹ የሚያደርግ ነው። በውጭ ምንዛሪ የሚካሄድ ኢ- መደበኛ ገበያ እየተስፋፋ በመምጣቱ አብዛኛው የንግድ ማህበረሰብና የሐዋላ ተገልጋዮች በአብዛኛው በጥቁር ገበያ ሲገዙና ሲሸጡ ይስተዋላል። አዲሱ የአስተዳደር ማሻሻያ ይህንን የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ ይሆናል።

ለፖሊሲው ስኬታማነት ለማረጋገጥም የሚከተሉት ቅድመ ዝግጅቶች ተከናውነዋል። በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል መንግሥት ከውጭ የሚገቡ የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ይደጎማል። በዚህም ነዳጅን፣ ማዳበሪያን፣ መድኃኒትና የምግብ ዘይትን የመሳሳሉ ከውጭ የሚገቡ የአራት መሠረታዊ ሸቀጦች የዋጋ ጫና በአንድ ጊዜ ወደ ሸማቹ እንዳይተላለፍ ወስኗል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ የዋጋ ንረት ምክንያት የእውነተኛ ገቢያቸው ዋጋ ለተሸረሸረባቸው ወገኖች የገንዘብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በዋጋ ንረት ምክንያት የደረሰውንና ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማርገብ ሲባል ያለውን የገንዘብ ምንጭ በመጠቀምና የመንግሥትን የበጀት ጉድለት በማያባብስ መልኩ ለመንግሥት ሠራተኞች የኑሮ ውድነት መደጎሚያ ደሞዝ ለመጨመር ታስቧል። እንዲሁም፣ በከተማም ሆነ በገጠር ለሚገኙ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚደረገው የሴፍቲኔት ርዳታ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል።

የመንግሥትን የማህበራዊ ወጪ ለመደገፍና ለውጭ ዕዳ ክፍያ የሚውለው ከፍተኛ የብር ወጪ ሌሎች ወጪዎችን በማይሻማ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ የውጭ ዕዳ ማቅለያ ርዳታ ተገኝቷል። ይህን መሰል ርዳታ ቀደም ብሎ መገኘቱ መንግሥት ለማህበራዊና ድህነት ተኮር ወጪዎች የሚያውለው የሀብት አመዳደብ እንዳይስተጓጎልና በቀጣይ ዓመታትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይረዳዋል።

በቀጣይ የሚወሰዱ ርምጃዎች የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ሥራ ላይ መዋል፣ ከሌሎች አጋዥ ማክሮ ርምጃዎች ጋር ተዳምሮ፣ ኢትዮጵያ ዕድገቷንና የወደፊት ብልጽግናዋን እንድታፋጥን አይነተኛ ዕድል ይሰጣታል። ቁልፍ የሆኑ መሰናክሎችንና አደናቃፊ እክሎችን በማስወገድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመጪዎቹ ዓመታት ትልቅ እመርታ እንደሚያሳይ ይጠበቃል። በዓለም የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ትንታኔ መሠረት፣ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የማሻሻያ ርምጃዎች ዕድገትን ለማፋጠን፣ የዋጋ ንረትን ለማርገብ፣ የፊስካል አቅምን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግድንና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

እንዲሁም በዚሁ ትንበያ መሠረት፣ በማሻሻያ ርምጃዎቹ ምክንያት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በስምንት በመቶ ያህል ያድጋል፤ የዋጋ ንረትም ወደ 10 በመቶ የተጠጋ ይሆናል፤ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 11 በመቶ ይደርሳል፣ የመንግሥት ዕዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ወደ 35 በመቶ ዝቅ ይላል፤ የወጪና የገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር ያድጋል፤ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ከፍ ይላል፤ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ይሆናል። እነዚህ ትንበያዎች በቀጣይ ዓመታት ከላይ በተጠቀሱት ማሻሻያዎች ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የኢኮኖሚ ሽግግር ደረጃ የሚያመለክቱ መሆናቸውን አቶ ማሞ ጠቁመዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በጎነትን ባህሏ ያደረገች ልበ ቀና ሴት

**አመለወርቅ ከበደ**

የሰው ልጅ አብዛኛውን ጊዜ በአካባቢው በሚመለከተው ነገር ማንነቱ እንደሚቀረጽ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ይናገራሉ። እናም ይህ የምናየው ነገር ቀስ በቀስ በአዕምሯችን ይቀረጻል። በጊዜ ሂደት ደግሞ እራሳችን የምንከውነው ተግባር እየሆነ ይመጣል።

ለዚህም ይመስላል አብዛኞቻችን ያሳደገን ማህበረሰብ ነጸብራቅ ነን የሚባለው። በቀጣይ ደግሞ እኛን ተከተው ለሚፈጠሩ ማህበረሰቦች እርሾ እንሆናለን። እንደዚህ እየሆነ የትውልድ ቅብብሎሽ ይቀጥላል።

ቢጠቅምም ባይጠቅም ደግነት ይሻላል ከክፋት እንዳለው ገጣሚ፤ ዛሬ በበጎነት በምንሰራው እያንዳንዷ ተግባር ለሌሎች መስታወት እየሆን ነው የምናልፈው።

የዛሬዋ ባለታሪካችን ወደ በጎ ሥራ እንድትገባ ምክንያት የሆናት ያሳደጋት ማህበረሰብ ነው። በአደገችበት አካባቢ አብሮ መብላትን፣ መረዳዳትን ስትመለከት በማደጓ በጎ ተግባርን ይዛው በማደግ ዛሬ ላይ የቀን ተቀን ተግባሯ አድርጋዋለች።

እራሷን ከማሳተፍ አልፋ ሌሎች እንዲሳተፉ በመጋበዝ በበጎ አድራጎት ሥራ በርካቶችን እየጠቀመች ትገኛለች።

የዛሬዋ ባለታሪካችን ወይዘሮ አፍራ አሕመድ ይባላሉ፤ ትውልድና እድገታቸው በድሬ ከተማ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት እዛው ድሬዳዋ ከተማ ነው።

‹‹የተወለድኩት በ1972 ዓ.ም ነው። ትምህርቴን እስከ 12ኛ ክፍል እዛው ድሬ ከተማ ነበር የተማርኩት። በትምህርቴ ጥሩ የምባል ዓይነት ተማሪ ብሆንም፣ እኛ አካባቢ ሴት ልጅ ቶሎ ስለምትዳር ተዳርኩኝ ›› ይላሉ።

በትዳርም ስድስት ልጆችን አፍርተዋል። ትምህርታቸውን በኮምፒውተር ሳይንስ በዲፕሎማ በማጠናቀቅ፤ ለሰባት ዓመት በሥራ ዓለም ቆይተዋል። አሁን ልጆቼ ቦታ ስለያዙ ሥራ አቁሜያለሁ የሚሉት ወይዘሮ አፍራ የራሳቸውን የግል ሥራ ለመሥራት እንደሚያቅዱ ይገልጻሉ።

ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው መኖር ከጀመሩ በኋላ በሚኖሩበት አካባቢ የተቸገሩትን በመርዳት የሚደርሳቸው አልነበርም። ከዛን እንደ ወረዳ በሚደረጉ የበጎ ተግባራት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ለ14 ዓመታት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እያገለገሉ ይገኛል። የበጎ አድራጎት ሥራ ከልጅነት ጀምሮ አብሯቸው ያደገ ተግባር እንደሆነም ይናገራሉ።

በልጅነታቸው በድሬዳዋ ከተማ በሚኖሩበት ወቅት በእድሜ ጠና ያሉ አሮጊቶች ሲታመሙ ሄደው በማስታመም ገላቸውን በማጠብ ይረዱ ነበር።

ይህ ባህሪያቸው ትዳር መስርተው አዲስ አበባ ከመጡም በኋላ አብሯቸው ቀጠለ። በአካባቢያቸው ሰው በሚታመምበት ወቅት፣ በማስታመም፣ ሴቶች ምጥ ሲይዛቸው ያላቸውን በማልበስ ወደ ሆስፒታል በመውሰድ ድጋፍ ያደርጉ ነበር።

የወይዘሮ አፍራ እርዳታ በዚህ ብቻ አልተገደበም። ደብተር ለመግዛት አቅም የሌላቸውን ተማሪዎች ደብተር በመግዛት፣ ለደብተር መያዣ ቦርሳ በመግዛት እና ከልጆቻቸው የተረፉ ልብሶች በመስጠት ይደግፉ ነበር። እንደዚህ ዓይነት ድጋፎች እያደረጉ በመጡ ቁጥር ልባቸው ለበጎ አድራጎት ሥራ ይበልጥ እየተሳበ መጣ።

ሰውን መርዳት በጣም ደስ የሚለኝና የተወለድኩበት ነው የሚሉት ወይዘሮ አፍራ፤ ይህን ሰው የመርዳት ተግባሬን ይፋ በሆነ መንገድ ለመሥራት በማሰብ ወረዳ ሄጄ ተመዘገብኩ ሲሉም ያስረዳሉ።

ሰውን መርዳት ቅንነት ነው፤ ሁለት ያለው አንዱን እንዲያካፍል ቁራንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለዚህ ማንም ምንም ሳይገድበው ሌሎችን መርዳት አለበት ይላሉ።

ድሬዳዋ እያለሁ ብቻችንን አንበላም በማለት ትውስታቸውን ይናገራሉ። ‹‹እናም ይህ ልማድ ከውስጤ ሊወጣ አልቻለም። አዲስ አበባ ከመጣሁ አሁን 24 ዓመቴ ነው። የበጎ ፈቃድ ሥራ አብሮኝ ያደገ በመሆኑ አዲስ አበባም መጥቼ በዚሁ ተግባር ቀጠልኩ›› ይላሉ ወይዘሮ አፍራ።

በወቅቱ ወረዳ ላይ ተመዝግበው የበጎ አድራጎት ሥራ በመሥራት የሚያስተባብሩ ሴቶች ስለነበሩ ወይዘሮ አፍራ ከእነሱ ጋር ትሳተፍ ስለነበር እየተግባቡ መጡ። ከዛ በኋላ በበጎ ፈቃድ ሥራ በስፋት መሳተፍ ጀመሩ።

ወይዘሮ አፍራ በክፍለ ከተማው የቤት እጦት



ወይዘሮ አፍራ አሕመድ

ፎቶ ገባቡ ገብሬ

ላለባቸው ሰዎች ባለሀብቱን በማስተባበር እና ያላቸውን በማዋጣት የቤት እድሳት ሥራ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በወረዳ ደረጃ ይሳተፋሉ።

በቤት እጦት የሚቸገሩ አዲስ አበባ ላይ በጣም በርካታ ናቸው። ክረምት ሲመጣ ጎርፍ የሚገባባቸው፣ የሚያፈስ ቤት ያላቸው እና አቅመ ደካሞች ብዙ መሆናቸውን በመግለጽ ይህን በማየት ነው ወደዚህ ተግባር የገባሁት ይላሉ።

‹‹የቤት እድሳት በሚደረግበት ወቅት በማፍረስ ሥራ ላይ እሳተፋለሁ፤ ብሎኬት በማቀበልም እረዳለሁ። አንድ ሰው ቅንነት ከውስጡ ካለ፤ አንድ ነገር ለማድረግ የሚከብደው ነገር የለም ›› ይላሉ።

ለዚህ እንደ ምሳሌ የሚያነሱት የአዲስ አበባን የኮሪደር ልማት ነው። ሥራው ሲጀመር አንዳንድ ሰዎች "ጀምረው ጭቃ አድርገው ሊተውቱ" በማለት አውርተው ነበር። ነገር ግን በጥቂት ጊዚያት ሊጠናቀቅ መቻሉ ለሁላችንም ትምህርት የሚሆን ነው። ሲሉ አንድ ነገር ከታሰበበት እንደማይከብድ ያስረዳሉ።

ለእናቶች የጡት ጫፍ ካንሰር በሽታ ምርመራ፣ ሕክምና ግንዛቤ በሚሰጥበት ወቅት በስፋት ተሳትፎ በማድረግ በርካታ ሴቶች፤ በራሳቸው ፈቃድ እንዲመረመሩና ግንዛቤ እንዲያገኙ አድርጋለች።

‹‹የበጎ አድራጎት ሥራ በመሥራቴ ተቆጥሮ የሚሰጠኝ ገንዘብ ባይኖርም፤ ማህበረሰቡን በመርዳቴ፤ በተለይም ሴቶች ከቤት ወጥተው እራሳቸው እንዲችሉ እና በዕሻራ ከመፈረም እንዲላቀቁ በማደረጌ በጣም ደስተኛ ነኝ›› ይላሉ።

ሴቶችን ለመርዳት ከሚያደርጉት ጥረት አንዱ ትምህርት ያላገኙ ሴቶች መሠረት ትምህርት እንዲያገኙ ቅስቀሳ ማድረግም ይገኝበታል። ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ሴቶች በማስተባበር በሥራ እንዲሳተፉ እና የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጠሩ ጥረት ማድረጋቸውም አልቀረም።

የበጎ አድራጎት ተግባራቸው በከተማው እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማት ሥራም ቀጥሏል። ወይዘሮ አፍራ ከጓደኞቿ ጋር በመሆን፤ በኮሪደር ልማት ሥራ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞችን እራት የማብላት ተግባርም ያከናውናሉ።

ይህ ሃሳብ እንዴት እንደመጣላቸው የሚናገሩት ወይዘሮ አፍራ፤ አንድ ምሽት ዝም ብዬ አየር ለመቀበል ወጣ እንዳልኩ መንገድ ላይ የሚሰሩት ውሃ ሲያጠጡ ተመለከትኩኝ። እናም እነዚህ ሰዎች ምግብ ማብላት እንዳለብን ሃሳብ መጣልኝ። ከዛን ባለሀብቶችንም በማስተባበር እራት አበላን ይላሉ።

መሸት ሲል በመውጣት ከፒያሳ ሜክሲኮ ከሜክሲኮ እስከ ወሎ ሰፈር የሚሰሩትን በጥሩ ሁኔታ ማብላት ችለናል። እስካሁን ሁለት ጊዜ ማብላታቸውን በመግለጽ፤ ለመቀጠል እቅድ እንዳላቸው ይገልጻሉ።

አፍራና ጓደኞቿ ይህ ተግባር የሰሩት በራሳቸው ተነሳሽነት ነው። በዚህም ሄደው እነዚህን ሠራተኞች በመጠየቃቸው በጣም ደስተኛ ናቸው። ክፍለ ከተማውም በሰሩት ሥራ ምስጋና ተቸሯቸዋል።

በአረንጓዴ ልማት ችግኝ በመትከል፣ በየሶስት ወር ደም በመለገስ እና በሳምንት አንዴ አካባቢያቸውን በማጽዳት ሥራም ይሳተፋሉ።

ወይዘሮ አፍራ የልጆች እናት እንደመሆናቸው ልጅ መንከባከብ በጎ ሥራን ወጥቶ ከመሥራት አላገዳቸውም። ለልጆቻቸው ሞግዚት ብዙ ጊዜ የሚቀጥሩ ሲሆን፤ የባለቤታቸው እገዛ እና ማበረታቻም አልተለያቸውም።

‹‹ባለቤቴ ጥሩ ሥራ ነው በርቺ ይለኛል። በዓል በሚሆንበት ወቅት ደግሞ ዘይት፣ ዱቄት እና ሌሎች ነገሮችን በመያዝ ማእድ እናጋራለን›› ሲሉ ይገልጻሉ።

‹‹ለበጎ አድራጎት ሥራ ስወጣ ልጆቼ ሲመለከቱ በጣም ደስ ይላቸዋል። በተለይ አንድ የሕክምና ትምህርት የምትከታተል ልጅ አለችኝ እሷ "አንቺ ዛሬ የምትሰሪው ሥራ ለእኛ ነው የሚተርፈው፤ በዚህ ሥራሽ እኛ የትም አንወድቅም" ትለኛለች። ወደፊት ልጆቼ የእኔን አርአያ ይከተላሉ የሚል ተስፋ አለኝ።›› የሚል ተስፋ ሰንቀዋል።

ወይዘሮ አፍራ የሕዳሴ ግድቡ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ለ13 ዓመታት ቦንድ ገዝተዋል። እሳቸው ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸውንም በዚህ ተግባር አሳትፈዋል።

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት ልጄ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወሰዶ ከፍተኛ ውጤት ስላመጣ ክፍለ ከተማ ጠርቶ ሽልማት ሰጠው። ሽልማቱን ተቀብለን ስንመለስ "ምን ላድርገው ብሩን? ቦንድ ልግዛበት?" ብሎ ጠየቀኝ። እንደውም ጥሩ ነገር ስለው እሱም ገዛ። ይህን ልምድ ልጆቼም ተጋርተውኛል ሲሉ ያስረዳሉ።

‹‹አጠገብ ላይ ሰው ተርቦ በር ዘግቶ ለብቻ መብላት ይከብዳል። አንዳንዴ እኮ ወጥ ሲሰራ ሽታው ጎረቤት እንዳይረብሽ በመሥጋት፣ አጣፍጦ ለመሥራት ይከብዳል። ነገር ግን እንደዚህ አካፍሎ መብላት ካለ የሥነ ልቦና ተፅእኖ አይኖርም። እናም ይህን ተግባር በማድረጌ በጣም ደስተኛ ነኝ›› ይላሉ።

ወ/ሮ አፍራ እንደሚሉት ሥራዎች የሚሰጡት ከወረዳው በሚወርደው አቅጣጫ መሠረት ነው። በበርካታ ሥራዎች እንደመሳተፋቸው ለእያንዳንዱ አዲስ ለሚመጡ አቅጣጫዎች ፕሮግራም በመያዝ ሁሉንም ለማስኬድ ይጥራሉ። ቤት ማሳደስ ፣ መሠረተ ትምህርት ላይ፣ የጡት ካንሰር ግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሌሎች ነገሮችን ተራ በማስያዝ በቅድመ ያከናውናሉ።

የበጎ ፈቃድ ሥራ የህሊና እርካታ ከማስገኘቱም በላይ የበርካቶችንም ችግር እየቀረፈ የሚገኝ ሰናይ ተግባር ነው የሚሉት ወ/ሮ አፍራ በአንድ የምንኖር ሰዎች ያለንን አብረን ተካፍለን ብንበላ ወደ ጎዳና ወጥቶ የሚለምን ሰው ባልኖረ ነበር ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ ሀገር ሆነ እንደ አዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ምንም ነገር ሳይፈሩ እንደዚህ ዓይነት በጎ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ሊሰሩ ይገባል። ሴቶች በመሆናችንም ምንም የሚገድበን የለም ሲሉ ለሌሎች ሴት እህቶቻቸው መልዕክት ያስተላልፋሉ።

በቀጣይም አሁን የጀመሩትን የበጎ አድራጎት ሥራ በማጠናከር፤ ጎዳና የወደቁ እናቶችና አባቶች ለመርዳት ሃሳብ አላቸው። በተጨማሪም የሕፃናት መዋያ በመክፈት ልጄን የት ላድርግ? እያሉ ለሚጨነቁ እናቶች መፍትሔ የመሆን ምኞች አላቸው።

የሕፃናት መዋያ ከፍታ በቅናሽ ዋጋ የምትሰራ ሴት አለች። እኔም በቀጣይ እንደዚህ ዓይነት ሕፃናት የሚውሉበትን ቦታ በማዘጋጀትና በመሥራት ፤ እናቶች ልጆቻቸውን ያለ ስጋት ትተው እንዲሄዱ እና ቀሪ ሥራቸውን እንዲሰሩ ማድረግ እፈልጋለሁ ሲሉ የወደፊት ዕቅዳቸውን ይገልጻሉ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

አንጋፋው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዘመናት ጉዞው ሰንዶ ለትውልድ ያሻገራቸው ዘገባዎቹ ዛሬ ላይ ታሪክ ናቸው። አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችንም በተለያዩ ዘመናት ጋዜጣው ለንባብ ያበቃቸውን ዘገባዎች እየቀነጨበ ለቅምሻ ያህል ያቀርብልናል። ለዛሬም በተለያዩ ዓመታት ለንባብ የበቁ የተለያዩ ዘገባዎችን እንደሚከተለው ያስታውሰናል።

**የሰላም ውይይቱ ተሳታፊ ቡድን ተሰየመ**

ተሳታፊዎች ገንቢ ሃሳብ ይዘው እንዲቀርቡ መንግሥታት ጥሪ አቀረቡ

**(ኢዜአ)፡-** በኢትዮጵያ መንግሥትና በተቃዋሚ ቡድኖች መካከል በመጪው ሰኞ ለንደን ላይ ተሳታፊ የሚሆነውን ቡድን የመንግሥት ምክር ቤት ሰየመ።

የሰላም ልዑካን ቡድኑን የሰየመው በጓድ ሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ አባልና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የመንግሥት ምክር ቤት ትናንት ከቀትር በፊት ባደረገው ስብሰባ ነው።

ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ ተለዋጭ አባልና ጠቅላይ ሚኒስትር የቡድኑ መሪ እንዲሆኑ በምክር ቤቱ ተሰይመዋል። በሀገራችን ያለው የወቅቱ እጅግ አሳሳቢ ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የብሔራዊ ሸንጎ 3ኛ አስቸኳይ ጉባዔ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረትና እንዲሁም የመንግሥት ምክር ቤት ሰሞኑን የመፍትሔ ሃሳቦችን ጨምሮ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከሁሉም በፊት ሰላም ይገኝ ዘንድ ለአፋጣኝ መፍትሔ በሚያደርገው ጥረት ለንደን ላይ የሚደረገው የሰላም ውይይት የተሳካ እንዲሆን በመድረኩ ላይ ተሳትፎ ለሚያደርገው ቡድን አስፈላጊውን መመሪያ ሠጥቷል።

መንግሥትን በመወከል በውይይቱ የሚሳተፈው ቡድን በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ የሚደረገው የእርስ በእርስ ጦርነት ቆሞ የሽግግር መንግሥት ይመሠረት ዘንድ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠርና ተገቢውን አስተዋፅኦ ለማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን የመንግሥት ምክር ቤት ገልጧል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 17 ቀን 1983 ዓም)**

**ስደተኞችና ከስደት የተመለሱት ስለሚረዱበት ሁኔታ ውይይት ተካሄደ**

**(ኢዜአ)፡-** ከሶማሊያ ተፈናቅለው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኞችና ከሶማሊያ ወደ ሀገራቸው የተመለሱትን ኢትዮጵያውያንን መርዳት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የተነጋገረ ስብሰባ ትናንት በማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ተካሂዷል።

ለስደተኞቹ ዕርዳታ የሚደርስበትን ሁኔታ የሚከታተለውና በቅርቡ የተቋቋመው የሶማሊያ ስደተኞች ድጋፍ ሰጪ ከፍተኛ ብሔራዊ ኮሚቴ ባዘጋጀው በዚሁ ስብሰባ ላይ የዓለም አቀፍ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ተወካዮች ተካፍለዋል።

ጓድ ሽመልስ አዱኛ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፤ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የኮሚቴው አስተባባሪ ለተሳታፊዎች ባደረጉት ገለጣ፤ የሶማሊያ ስደተኞችንና ወደ ሀገራቸው የተመለሱትን ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት እስካሁን መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በመተባበር ያልተቆጠበ ድጋፍ ሲሰጥ መቆየቱን አውስተው፤ ለተልዕለኮውም መሳካት የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ሲያደርግ የነበረውን ትብብር ገልጠዋል።

በአሁኑ ወቅትም በቂ ምግብ ውሃ መጠለያና መድኃኒት ለማቅረብ ከርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ያልተቆጠበ ትብብርና ድጋፍ እንደሚያስፈልግ አመልክተው በተለይም ለዚሁ አቅርቦት የወሳኝነት ሚና ያለው የትራንስፖርት ችግር መቃለልና አፋጣኝ መፍትሔ ማግኘት እንደሚገባው አስረድተዋል።

ቀደም ሲል በተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር የአፍሪካ አህጉር ተወካዮች፤ ከሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካዮች ጋር በመሆን በሥፍራው ባደረጓቸው ጉብኝቶች የጉዳዩን አሳሳቢነት መጠቆማቸውን ጓድ ሚኒስትሩ ገልጠው፤ ይህን ችግር አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኝ ዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ያላሰለሰ ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበዋል። ከሰማሊያ ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሶማሊያ ስደተኞች 640 ሺህ ሲሆኑ ወደ ሀገራቸው የተመለሱት ኢትዮጵያውያን ደግሞ 246 ሺህ ናቸው።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 17 ቀን 1983 ዓ‡ም)**

**በዋጋ ንረትና ሥርጭት መዛባት ጉዳይ ላይ ውይይት ተካሄደ**

(ኢዜአ)፤ ሀገራችን አሁን የምትገኝበት እጅግ አሳሳቢ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ በተከሰተው የዋጋ ንረትና የሥርጭት መዛባት ጉዳይ ላይ በንግዱ ዘርፍ ከተሰማራው ኅብረተሰብ ጋር ተወያይቶ ጋራ ግንዛቤ ለመውሰድና መፍትሔ ለመፈለግ የሚያስችል ስብሰባ ትናንት ተካሂዷል።

ጓድ ግዛው ንጉሤ የአዲስ አበባ አካባቢ ዋና አስተዳደር በዚሁ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ፤ ወያኔ ሀገርን ለመከፋፈል በየአካባቢው በከፈተው ጦርነት ምክንያት የተናጋው የኅብረተሰቡ ሰላምና አንድነት ለማስከበር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሚያካሂድበት በአሁኑ ወቅት ነጋዴው በምርቶችና ሸቀጦች ላይ ዋጋ ከመጨመር እንዲቆጠብ አሳስበዋል።

መንግሥት የንግዱ ኢኮኖሚ መስክ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ ፤ እንዲመራና ለአጠቃላይ ኅብረተሰብም ሆነ በዘርፍ ለተሰማራው ዜጋ የተሻለ ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ጓድ ግዛው ጠቅሰው ፤ ከየወቅቱ ፍላጐትና በተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ፖሊሲዎችን፤ ሕጎችን ፤ መመሪያዎችንና ደንቦችን አውጥቶ ሥራ ላይ በማዋል ንግዱ ከግብታዊነት ተላቆ የተሻለ ሥርዓት እንዲይዝ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስረድተዋል።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 24 ቀን 1983)**

**ሽፍቶችን ለማስወገድ ፈቃድ ጠየቁ**

ሐረር ፤ በውጋዴን ግዛት የሚገኙ ባላባቶች ሁሉ ከየጐሣቸው አንዳንድ ታላላቅ ባላባቶች ወደ ሐረር በመላክ ሽፍቶቹ በሀገራቸው ላይ ስለሚያደርጉት ጉዳት አሳባቸውን ለጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ለክቡር ሌተና ኰሎኔል ታምራት ይገዙ እንዲገልጹላቸው አድርገዋል ፤ የተላኩት ባላባቶችም መስከረም ፫ ቀን ፶፮ ዓ.ም. ወደ ክቡር እንደራሴ ቀርበው የተሰጣቸውን እምነትና አደራ የረሱ ከሃዲዎች በሀገራችን ላይ በመሸፈት ሀገራችንን ከማጥፋት በላይ በንብረታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስላደረሱብን ተባብረን ለማጥፋት ቆርጠን የተነሳን ስለሆነ ፤ መንግሥታችን ይህንኑ እንዲፈቅድልን እንለምናለን ። ሽፍቶቹም ተወላጆቻችን አይደሉም በማለት አሳባቸውን ገልጸውላቸዋል።

ክቡር እንደራሴውም አሳባቸውን ካዳመጡ በኋላ ፤ ሰው ሆኖ የማያጠፋ የለም ፤ ቢቻል በምክር ውንብድነታቸውን ቢተዉ ምከሩአቸው ፤ ካልሆነ እያንዳንዳቸው እጃቸውን እየያዛችሁ ለመንግሥታችሁ ብታስረክቡ መልካም ነው ፤ በማለት መልስ ስለሰጡዋቸው ምስጋናቸውን አቅርበው ተመልሰዋል ። ከባላባቶችም የቀብሪ ደሐር አውራጃ ግዛት ሕዝብ እንደራሴ ቀኛዝማች አሙመር ባራሌ ፤ የቀላፎ አውራጃ ገዥ ቀኛዝማች በሽር ሴክ አብዲ ፤ የፊርፊር ወረዳ ግዛት አቶ መሐመድ ባሂር ሌሎችም እነሱን የመሳሰሉ ተገኝተው ነበር ሲል በጠቅላይ ግዛቱ የሚገኘው ወኪላችን አስታውቋል ።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 5 ቀን 1956 ዓ.ም)**

**ሽማግሌው ሞተው ተገኙ**

አድዋ፤ (ኢ-ዜ-አ-) በአድዋ አውራጃ ግዛት በአዲ አቤቶ ወረዳ እንዳ ማርያም ውኢላ በተባለው ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ለ፳፭ አጥቢያ ለጊዜው አድራሻቸውና ስማቸው ያልታወቀ አንድ ሽማግሌ ሞተው ተገኙ።

የሰውየውን መሞት የቀበሌው ሕዝብ ለፖሊስ ጣቢያ ካመለከተ በኋላ ፤ አስከሬኑ አዲአቡን ወደሚገኘው መንገሻ ዮሐንስ ሆስፒታል ተወስዶ ሽማግሌው በሰው እጅ ያልሞቱ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ፤ ደብረማርቆስ ቤተክርስቲያን ተቀብሯል። የሟቹ ዕድሜ ፷፰ ዓመት እንደሚሆን ተገምቷል።

**(አዲስ ዘመን ጥር 7 ቀን 1961 ዓም )**

# ዓለም አቀፍ

## በእስራኤል እና ሔዝቦላህ መካከል እየተባባሰ የመጣው ግጭት ሊባኖሳውያንን አስጨንቋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ካለፈው ጥቅምት ጀምሮ በእስራኤል እና በኢራን በሚደገፈው የሊባኖሱ ታጣቂ ቡድን ሔዝቦላህ መካከል ያለው ውጥረት እና ግጭት እየተባባሰ መጥቷል።

በግጭት ምክንያት በሁለቱም ወገን የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ በርካታ ሺዎች ደግሞ ቤት ንብረታቸው ጥለው ለመሰደድ ተገደዋል።

ይህ ግጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተካረረ የመጣ ሲሆን ወደለየለት ጦርነት ይገባል የሚል ስጋት አለ።

ምንም እንኳ ሁለቱ ኃይሎች በጥቃትና በመልሶ ማጥቃት ቢወጠሩም ከባድ የሚባል ጦርነት ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ሲያደርጉ ይስተዋላል።

ነገር ግን ባለፈው ቅዳሜ በእስራኤል ቁጥጥር ሥር ባለችው ጎላን ሀይትስ በተሰኘችው ሥፍራው የደረሰው ጥቃት ሁለቱ ኃይሎች ወደ ደም አፋሳሽ ጦርነት ይገባሉ የሚል ጥርጣሬ ጭሯል።

እስራኤል ድሩዝ ከተማ ባለ አንድ የእግር ኳስ ሜዳ ላይ ደርሶ ሕፃናትን ጨምሮ 12 ሰዎችን የገደለውን ጥቃት ያደረሰው ሔዝቦላህ ነው ስትል ትወቅሳለች። እስራኤል ለዚህ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት ቃል ገብታለች።

"እስራኤል ይህን ጥቃት በዋዛ የምታልፈው አይደለም" ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታኒያሁ በቢሯቸው በኩል በለቀቁት መግለጫ አስታውቀዋል።

"ሔዝቦላህ እስከዛሬ ድረስ ከፍሎት የማያውቀውን ዋጋ ይከፍላታል" ሲሉም ዝተዋል። ነገር ግን ሔዝቦላህ የተባለው የሌባኖሱ ታጣቂ ኃይል ጥቃቱን አላደረስኩም ሲል ያስተባብላል።

ቢሆንም ቡድኑ ሔርሞን የተባለውን ብሪጌድ በኢራን ሰራሽ ፋላቅ ሚሳዔል መምታቱን የገለጠ ሲሆን ቅዳሜ ዕለት ከደረሱ በርካታ ጥቃቶች አንዱ ነው። ድሩዝ የምትባለው ከተማ ከሔርሞን ተራራ 3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ሔዝቦላህ ምናልባት ዒላማውን ስቶ ሊሆን ይችላል የሚሉ መላ ምቶች እየተሰሙ ነው።

የእስራኤል ጦር ሠራዊት ቃል አቀባይ ዳንኤል ሐጋሪ፤ ቡድኑን ጥቃቱን ማስተባበሉ "ሐሰት" ነው ብለው የስለላ መረጃዎች የሚያሳዩት ጥቃቱ የተሰነዘረው በሔዝቦላህ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

"ሁሉም ነገር የሚጠቁመው" ሚሳዔሉ የተተኮሰው በሔዝቦላህ ነው ሲሉ የተናገሩት የዩኤስ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በበኩላቸው "እስራኤል በምታደርገው ራሷን የመከላከል ርምጃ አሜሪካ ከጎኗ ትቆማለች" ብለዋል።

በዚህ ምክንያት ሌባኖስ ከእስራኤል የመልሶ ማጥቃት ርምጃ ይሰነዘራል በሚል ፍራቻ ላይ ትገኛለች። ሔዝቦላህ እስራኤል ላይ ጥቃት ማድረስ የጀመረው በአውሮፓውያኑ ጥቅምት 8 ሲሆን ከአንድ ቀን በፊት የፍልስጤሙ ሐማስ ያደረሰውን ጥቃት በመደገፍ እንደሆነ አስታውቋል።

እስካሁን በሁለቱ ኃይሎች መካከል በተከሰተ ግጭት 450 ሊባኖስ ውስጥ ሲገደሉ 350ዎቹ የሔዝቦላ ታጣቂዎች ሲሆኑ 100 ደግሞ ሰላማዊ ነዋሪዎች ናቸው። በእስራኤል በኩል ደግሞ 23 ሰላማዊ ሰዎች ሲገደሉ 17 ወታደሮች በጥቃቱ ሞተዋል።

ሊባኖስ ውስጥ የደረሱት ጥቃቶች አብዛኞዎቹ ጥቃቶች የሀገሪቱን ደቡባዊ ክፍል ዒላማ ያደረጉ ናቸው። በተለይ ሔዝቦላህ በሚንቀሳቀስባቸው ቤካ ስምጥ ሸለቆ በተባለው አካባቢ እስራኤል ባደረሰችው ጥቃት መንደሮች ሲወድሙ በርካቶች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ሸሽተዋል።

እስራኤል እስካሁን ዒላማ ያልተደረጉ ዋና ከተማዋ ቤይሩትን ጨምሮ ትላልቅ የሚባሉ ከተማዎችን ልትመታ ትችላለች የሚለው ሃሳብ ግጭቱ ወደለየለት ጦርነት እንዳያመራ ስጋት ሆኗል።


ከሐማስ የበለጠ የተደራጀ ኃይል አለው የሚባለው ሔዝቦላህ በአውሮፓውያኑ 2006 ከተከሰተው ግጭት በኋላ ከእስራኤል ጋር ከባድ ጦርነት ለመግጠም ዝግጅት እያደረገ ቆይቷል።

ምዕራባውያን ሀገራት እንደሚሉት ቡድኑ 150 ሺህ ሮኬቶች እና ሚሳዔሎች የታጠቀ ሲሆን የእስራኤልን የተወሳሰበ የአየር መከላከያ ሊፈትነው ይችላል የሚል ግምት አለ። ቡድኑ፤ የእስራኤል ዋና ዋና ከተማዎች ማጥቃት የሚችሉ ዒላማቸውን የማይስቱ ሚሳዔሎች እንዳሉት ይነገራል።

በሁለቱ መካከል የሚነሳ ግጭት ሁለቱንም ሀገራት የሚጎዳ እንደሆነ ባይካድም በተለይ ባለፉት አስርት ዓመታት አለመረጋጋት ላይ ላለችው ሊባኖስ አደጋ ሊሆን ይችላል።

ዲፕሎማቶች በሁለቱ ኃይሎች መካከል ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። የሌባኖሱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አብደላህ ቦ ሐቢብ፤ ባለሥልጣናት ሔዝባላህ "መልሶ ማጥቃት እንዳይፈፅም እየጠየቁ ነበር" ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

# ስፖርት



# በፓሪስ ይደምቃሉ ተብለው የሚጠበቁ ኢትዮጵያውያን ከዋክብት

ብርሃን ፈይሳ

ኦሊምፒክን ለሶስተኛ ጊዜ የማስተናገድ ዕድል ባገኘችው ፓሪስ ውድድሮች መካሄድ ከጀመሩ አምስት ቀናት ተቆጥረዋል። እስካሁንም ሀገራት በተለያዩ ስፖርቶች ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ በደረጃ ሰንጠረዡ ላይ እየተፎካከሩ ይገኛሉ። ግብጽ እና ደቡብ አፍሪካን የመሳሰሉ ሀገራትም ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚዎቹ መሆን ችለዋል። በመጪው ሐሙስ በሚጀምሩት የአትሌቲክስ ውድድሮች ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የአህጉሪቱ ጠንካራ ተፎካካሪዎችም ወደ ሜዳሊያ ሽሚያው እንደሚገቡ ይጠበቃል።

ኢትዮጵያ ዘንድሮ 15ኛ የኦሊምፒክ ተሳትፎዋን የምታደርግ ሲሆን፤ የፓሪስ ኦሊምፒክ ውድድሯንም ከነገ በስቲያ በሚካሄደው የወንዶች 20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ የምትጀምር ይሆናል። በውሃ ዋና እና በአትሌቲክስ ስፖርቶች ተሳትፎዋን የምታደርገው ኢትዮጵያ በ43 በሚሆኑ አትሌቶች (ከእነተጠባባቂዎቻቸው) ትወከላለች። እነዚህም ርቀቶች በ800 ሜትር ሴቶች፣ 20 ኪሎ ሜትር የወንዶች ርምጃ እንዲሁም በሁለቱም ጾታ በ 1 ሺህ 500 ሜትር፣ 3ሺህ ሜትር መሰናክል፣ 5ሺህ ሜትር፣ 10ሺ ሜትር እንዲሁም በማራቶን ናቸው። ባለፉት ተሳትፎዎቿ 23 የወርቅ፣ 12 የብር እና 23 የነሃስ በጥቅሉ 58 ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ የቻለችው ኢትዮጵያ፤ በዚህ ኦሊምፒክም በምትታወቅባቸው የመካከለኛ እና የረጅም ርቀት ውድድሮች ተጨማሪ ክብሮችን ታስመዘግባለችም ተብሎ ይጠበቃል።

ከአራት ዓመታት በፊት ቶኪዮ ላይ በተካሄደው ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ በወንዶች 10ሺህ ሜትር በአትሌት ሰለሞን ባረጋ በተገኘው ብቸኛ የወርቅ ሜዳሊያ




በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በፓሪስ ኦሊምፒክ ለወርቅ ሜዳሊያ ታጭተዋል፣

እንዲሁም 1ብር እና ሁለት ነሃስ በጥቅሉ 4 ሜዳሊያዎች መመለሷ ይታወሳል። የፓሪስ ኦሊምፒክን ተከትሎ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አስቀድሞ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ቡድኑ ሊያስመዘግብ ያቀደውን ሜዳሊያ በቁጥር በይፋ አለመናገሩ የሚታወስ ነው። ይሁንና ቡድኑ እንደተለመደው በሚሳተፍባቸው የተለያዩ ርቀቶች ሜዳሊያዎችን ያስመዘግባል ተብሎ ተስፋ ተደርጎበታል። ኢትዮጵያ የኦሊምፒክ እና የዓለም ቻምፒዮናዎችን እንዲሁም የዓለም ክብረወሰን ባለቤት የሆኑ ምርጥ አትሌቶችን መያዟ የዚህ ተስፋ ምክንያት ነው።

ከታላቁ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ ቀዳሚው የወርቅ ሜዳሊያ አንስቶ እስካሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ስም የሚነሳው በጠንካራ አትሌቶቿ ነው። ከሀገር አልፈው በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ አዳዲስ ታሪክ እንዳጻፉት አንጋፋዎቻቸው አሁንም የዓለም አትሌቲክስ ቤተሰብ የወጣት አትሌቶቹን ብቃት ሊያይ ይጓጓል። ቶኪዮ ላይ ጠንካራዎቹን የዩጋንዳ አትሌቶች ጆሹዋ ቺፕቴጊን እና ጃኮፕ ኪፕሊሞን አስከትሎ የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀው አትሌት ሰለሞን ባረጋ ፓሪስ ላይም እጅግ ተጠባቂው አትሌት ነው። የ 10 ሺህ ሜትር ርቀትን የሚመራው ወጣቱ አትሌት ባለፉት የዓለም ቻምፒዮናዎች ላይ እንደተጠበቀው ባይገኝም በዚህ ዓመት ካለበት አቋም አንጻር ለሜዳሊያው የሚፎካከር ይሆናል። የቡድን አጋሮቹ ዮሚፍ ቀጄልቻ እና በሪሁ አረጋዊም ለተፎካካሪዎቻቸው የማይመለሱ አትሌቶች መሆናቸው ይታወቃል።

በሴቶች በዚሁ ርቀት ባለፈው ዓመት ቡዳፔስት ላይ የዓለም ቻምፒዮና የሆነችው አትሌት ጉዳፍ ጸጋይም ቡድኑ ካካተታቸውና ለተፎካካሪዎቻቸውም ስጋት ከሆኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አንዷ ናት። አትሌቷ በ5ሺህ ሜትር ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ ነሃስ ማጥለቋ የሚታወስ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት ደግሞ የዓለም ክብረወሰንን በመስበር የርቀቱ ምርጥ አትሌትነቷን አስመስክራለች። ጠንካራዋ አትሌት በ1 ሺህ 500 ሜትርም የቤት ውስጥ ክብረወሰን ባለቤት ስትሆን በሁለቱ ርቀቶች ሀገሯን ወክላ ኦሊምፒክ ላይ ትሮጣለች። በእርግጥ ከኬንያ እና ኔዘርላንድ በኩል እጅግ ፈታኝ ፉክክር እንደሚገጥማት ቢጠበቅም ከወጣቶቹ የቡድን አጋሮቿ ጋር በመሆን ሁለትና ከዚያ በላይ ሜዳሊያዎች ለኢትዮጵያ ይመዘገባሉ በሚል ይጠበቃል።

ሌላኛው የዓለም ክብረወሰወን ባለቤትና በርቀቱም ተስፋ ከሚጣልባቸው አትሌቶች መካከል የሚመደበው የ3ሺህ ሜትር መሰናክል አትሌቱ ለሜቻ ግርማ ነው። ኢትዮጵያ ከጥቂት ሜዳሊያዎች ያለፈ ስኬት ባላስመዘገበችበት በዚህ ርቀት የተገኘው ይህ አትሌት በቶኪዮ የብር ሜዳሊያን ያጠለቀ ቢሆንም፤ ከሶስት ተከታታይ የዓለም ቻምፒዮና ተሳትፎ በኋላ በመድረኩ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ለራሱና ለሀገሩ እንደሚያስመዘግብ ይጠበቃል።

በዚህ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ የምትጠበቅበት ሌላኛው ርቀት ማራቶን ሲሆን በሁለቱም ጾታዎች የሚኖረው ፉክክርም ከወዲሁ አጓጊ ሆኗል። በሴቶች የዓለም ክብረወሰን ባለቤት የሆነችውን ትዕግስት አሰፋ እና የዓለም ቻምፒዮናዋ አማኔ በሪሶ ያሉበት ይህ ቡድን በጠንካራነቱ ምናልባትም በርቀቱ ተሳታፊዎች ቀዳሚው ሊያደርገው ይችላል። በተመሳሳይ በወንዶች በኩልም የቀድሞው የኦሊምፒክ ኮከብ ቀነኒሳ በቀለ ወደ መድረኩ መመለስ እንዲሁም የኬንያዊው ድንቅ አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ በአንድ ውድድር መገናኘት በአትሌቲክ ስፖርት ታሪካዊ ሁነት ተብሎም ሊመዘገብ የሚችል ነው።

## ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

# ሠብዓዊነትን ታሳቢ ያደረገው ሠብዓዊ ድጋፍ

ሰላማዊት ውቤ

‹‹ሲያልቅ አያምር…›› ብለው ጀምረው ስለራሳቸውና በማህበሩ ተጠልለው ስለሚገኙ ወገኖች ሊያወጉን ሞከሩ። መጨረስ ግን አልቻሉም። ወጋቸውን በዚህ መልኩ መጀመራቸው የዛሬን አያድርገውና እሳቸውን ጨምሮ አብዛኞቹ በመጠለያው የሚገኙት እናቶች በቀደመው ጊዜ ቤት ንብረታቸው የሞላ ስለነበረ ነው። ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ይተርፉ ነበር።

ሆኖም አሁን መጠለያ የገቡት ጎዳና እና ባዶ ቤት ወድቀው በመገኘታቸው ነው። አረጋዊት ለምለም ወሸዬ የዕድሜ ጫናና ህመም ተዳምሮ አቅም ስላሳጧቸው ሰውነታቸው ብቻ ሳይሆን አንደበታቸውም አልታዘዘላቸው በማለቱ ወጋቸውን አልቀጠሉልንም።

ማንኛውም እንክብካቤ የሚደረግላቸው በማህበሩ ነው። ራሳቸው መፀዳዳት ስለማይችሉ ዳይፐር የሚቀይሩላቸው ማህበሩ የቀጠራቸው ተንከባካቢዎች ናቸው። ማንኛውንም የንጽህናቸው ጉዳይም የሚያልቀው በጽዳት ሠራተኞች ነው።

የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማህበር ውስጥ እኚህን እናት የመሰሉ 260 ወገኖች በማምሻ ዕድሜያቸው ተጠልለው ይገኛሉ። በነርቭና በተለያዩ የጤና ችግሮች ሳቢያ በራሳቸው ተንቀሳቅሰው መፀዳዳት የማይችሉት ብዙ ናቸው። እንዳስተዋልናቸው በዊልቸር የሚንቀሳቀሱ ቢኖሩም ከ90 በመቶው በላይ የሚሆኑት በየትኛውም ዓይነት ሁኔታ የተንከባካቢዎቻቸውን ርዳታ የሚፈልጉ ናቸው።

ከእነዚህ መካከል የነርቭ የጤና ችግር ያለባቸው አቶ ጥላሁን ዓለሙ አንዱ ናቸው። ከተኙበት ቀና ማለት አይችሉም። ባሉበት ሁኔታ ወደ ግራም ሆነ ወደቀኝ የሚያገላብጧቸው ፣ የሚያጎርሷቸው፤ የሚያፀዳዷቸው ተንከባካቢዎቻቸው ናቸው። እንደነገሩን እሳቸውም ጥሩ ሥራና ደሞዝ፤ ቤት፤ ንብረትና ቤተሰብ ነበራቸው። ሁሉንም በበሽታቸው ምክንያት አጥተውት ጎዳና ወድቀው ነበር። ማህበሩ ከወደቁበት ስላነሳቸውና አሁን ስላሉበት ሁኔታ ፈጣሪያቸውንም ደጋግመው ሲያመሰግኑ ይደመጣሉ።

በሙሉ እጅና እግር ይዞ እየተሯሯጠ ፈጣሪውን የሚያማርር በበዛበት ሁኔታ የእሳቸው ማመስገን ያስደምማል። አቶ ጥላሁን ባሉበት ሁኔታ ሆነው ወጣቱ ትውልድ ከአረጋውያን መማር ስላለበት፤ ይመክራሉ። አጠገባቸው ባለ አልጋ ላይ በከፋ የጤና ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ያበረታታሉ።

‹‹በባዶ ቤት ሞተው የሚገኙ፤ መንገድ ላይ ወድቀው የሚያነሳቸው ያጡ ወገኖች ባሉበት በዚህ ወቅት እሳቸው መጠለያ ውስጥ ክብካቤ እየተደረገላቸው በመገኘታቸው ማመስገናቸው ተገቢ ነው›› የሚሉት የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማህበር መሥራች አቶ ስንታየሁ አበጀ ናቸው።

አቶ ስንታየሁ ስለራሳቸው እንደነገሩን እናታቸው በልጅነታቸው ሲያርፉ በ1981 ዓ.ም ነው ከደቡብ ጎንደር ወደ አዲስ አበባ የመጡት። ሦስት ጊዜ ጎዳናና ባዶ ቤት ውስጥ ለመኖር ተገድደዋል። ብዙ መከራና ስቃይ ተፈራርቆባቸዋል። ማህበሩን መስርቶ እሳቸው ባለፉበት መንገድ የሚያልፉ ወገኖችን መደገፍ ያስፈለጋቸውም ለዚህ እንደሆነ ይናገራሉ።

አቶ ስንታየሁ እንዳጫወቱን በ1982ዓ.ም ጉበት፤ ኩላሊት እና ሌሎች በሽታዎች እሳቸው እርኩስ መንፈስ የሚሏቸው በሽታዎች ነበሩባቸው። ጉበታቸው ውሃ ከመቋጠሩም በላይ የአእምሮ ጭንቀት ስለነበረባቸው ሰው አገለላቸው። ለምኖ እንደሚበላ ስለማያውቁ ከህመሙ ጋር ተዳምሮ አራት ኪሎ ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን አካባቢ በጠኔ ምክንያት አካላቸው አልታዘዝ አላቸው።

ይህንን ተመለከተ አንድ ግለሰብ አነሳቸውና አሁን የወደቁትን አንሱ የነዳያን መርጃ ማህበር ያለበት ቦታ አስጠጋቸው። ድነው ሰው ቤት መሥራት ቢጀምሩም በ1983 ዓ.ም ተመሳሳይ የጤና ችግር ደርሶባቸው ተመልሰው ጎዳና ወጡ። በዚህ መልኩ ሦስት ጊዜ ወደ ጎዳና ለመውጣት ተገደዋል። በመካከል ሰዎች እያነሱ አስታምመው እያዳኑ ሰው ቤት ያስገቧቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

መጨረሻ ያስጠጋቸው ሰው ቤት ገዝቶ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ በህመም ምክንያት እግርና እጃቸው ደረቀ፤ ሌላ ባዕድ ነገር ከእግራቸው መውጣት ጀመረ። ጉንዳንና አይጥ አስቸግራቸው። ጎረቤት ዛሬም አልሞተም እስኪላቸው ደረሱ። ይሄንን ሁሉ መከራ አሳልፈው 2ሺህ 924 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረውን የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማህበር ለመመሥረት በቁ።




ማህበሩ አሁን ላይ 260 ወገኖችን ሙሉ እንክብካቤ በማድረግ፤ 150 ወገኖችን ደግሞ በውጭ ምግብና አልባሳታቸውን በመሸፈን ይደግፋል። በቅርቡ ለማህበሩ ከተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ኤምባሲ (UAE) ጋር በመተባበር 1 ሚሊዮን 60 ሺህ ብር የሚገመት የአልባሳት ድጋፍ ያደረገው የኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ሐረጓ ማሞ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ለተቸገሩ ወገኖች እያደረገ ያለው ድጋፍና እንክብካቤ የሚበረታታ ነው ብለዋል።

ማህበሩ ሴቶች፤ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንን ሌሎች ድጋፍ የሚሹ ወገኖችን ከወደቁበት ሰብስቦ በማስጠለል የሚንከባከብ በመሆኑ ትኩረት ሊቸረው እንደሚገባም አሳስበዋል። ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለ ማህበር በመሆኑ በክረምት ወቅት የሚለበሱ የብርድ ልብሶችና ቱታዎች እንደተበረከቱለት አንስተዋል። ድጋፉ የማህበሩን በጎ ተግባር አጠናክሮ ለማስቀጠልና ለማበረታታት ማለሙንም ጠቅሰዋል።

ወይዘሮ ሐረጓ ሠብዓዊነት ያለው ተመሳሳይ በጎ ተግባር በማከናወን ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኘው ሙዳይ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሌላው የአልባሳት ድጋፉ ተቋዳሽ ስለመሆኑም አስረድተዋል። ድጋፉ በተቋሙ አስተባባሪነት "በጎነትና አብሮነት ለኢትዮጵያ ከፍታ!" በሚል መሪ ሃሳብ በመላ ሀገሪቱ እየተካሄደ ያለው የዘንድሮ የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አካል ስለመሆኑም አውስተዋል።

በአልባሳት ርክክቡ ወቅት የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ኤምባሲ የዜጎች ጉዳይ ኃላፊ ወ/ሮ ዋፋ አህመድ ተገኝተዋል። ኃላፊዋ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ያሉ እንደነዚህ ያሉ ተቋማት ኤምባሲው ከሚኒስቴር መሥርያ ቤቱ ጋር በጋራ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰዋል። ድጋፎቹን ወደፊትም አጠናክሮ የሚቀጥል ስለመሆኑም ቃል ገብተዋል።